ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 343 ነሐሴ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



## የናይል ተፋሰስ ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ዕውነታ

ተስፋ ፈሩ

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ የናይል ወንዝ ውሃን በትብብር በማልማት መጠቀም እንዲቻል እ.አ.አ በ1997 የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ እንዲቋቋም ቁልፍ ሚና ተጫውታለች፡፡ ኢኒሼቲቩ ከተቋቋመ በኋላም የላይኛውን ተፋሰስ ሀገራት አስተባብራ ሂደቱ ለሁሉም የተፋሰሱ አባላት ፍትሐዊ የሆነ መብትና ግዴታ ይዞ እንዲወጣ ለማድረግ ሰፊ ጥረት አድርጋለች።

የኢትዮጵያ ጥረት ፍሬ አፍርቶ ኢኒሼቲቩ እ.አ.አ 2010 በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ፍትሐዊ የውሃ ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችለውን ሁሉን አቀፍ የናይል የስምምነት ማዕቀፍ ይፋ አድርጓል፡፡ የዚህ ስምምነት የመጀመሪያ ፈራሚ ሀገርም ኢትዮጵያ ናት፡፡

እ.አ.አ በ2013 የተፈረመውን ስምምነት በፓርላማ በማጸደቅ ረገድም ቀዳሚዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት፡፡ በመቀጠል ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳና ብሩንዲ አጽድቀውታል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ያጸደቀች 6ኛዋ ሀገር መሆንን ተከትሎ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን እውን ለመሆን ጫፍ ደርሷል፡፡

ስምምነቱን የማጽደቁ ሂደት ሀገራቱ በእራሳቸው የሚያከናውኑት ተግባር ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ሁሉም ሀገራት ስምምነቱን በፍጥነት እንዲያጸድቁ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ሥትሠራ ቆይታለች፡፡

የምሥራቅ ናይል አካባቢ ቀጣናዊ የቴክኒክ ጽህፈት ቤት ምክትል ዳይሬክተር ሆነው ያገለገሉት የውሃ ሀብት አስተዳደር አማካሪው

የናይል ተፋሰስ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







## የውሃ ጥም ቆራጩ- የጉምቢ ቦርደዴው ፕሮጀክት

አስቴር ኤልያስ

**ዜና ሐተታ**

ወቅቱ ክረምት ቢሆንም በአካባቢው የጭጋግ ምልክትም ሆነ ዝናብ አይታይም።

ነገር ግን በአግባቡ ላስተዋለ ፣ የሰውንም የከብቱንም ሆነ የመሬቱን ጥም የቆረጠ ውሃ ከርቀት ተንጣሎ ይታያል - በኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በጉምቢ ቦርደዴ ወረዳ በፊና ኢትዮጵያ የተገነባው የጎዳ ጨሌ ግድብ

የውሃ ጥም ቆራጩ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ቁልፍ ሀገራዊ ጉዳዮች የሚሰበሰቡበት የምክክር ሂደት



ማህሌት ብዙነህ

**ዜና ትንታኔ**

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሀገሪቱ የተፈጠሩ አለመግባባቶችንና የሃሳብ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ በቀጣይ ዓመት ያካሂዳል። በምዕራፍ የተከፋፈሉና ለምክክሩ የሚያስፈልጉ ሂደቶችን የማከናወን ሥራዎች ከተጀመሩ ደግሞ ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል፡፡

በእነዚህ ሁለት ዓመታት ውስጥም በምክክር ሂደቱ ላይ ተሳታፊዎችን የመምረጥ ሥራ በተለያዩ አካባቢዎች ተከናውኗል። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች የምክክር ሂደቱ ወሳኝ ሚና ያለው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ እየተካሄደ ይገኛል። በመዲናዋና በጋምቤላ የተካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ደግሞ በድሬዳዋና በተለያዩ አካባቢዎች ቀጥሏል።

ታዲያ ይህ የምክክር አጀንዳ በምን መልኩ ይዘጋጃል፤ ምንስ ያካትታል? ለምክክር ሂደቱስ ምን አስተዋጽኦ ይኖረዋል? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ኮሚሽነሮችና አማካሪዎች አነጋግረን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም እንደሚገልጹት፤ የሀገራዊ ምክክሩ ሂደት ከሚጠይቃቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል አጀንዳዎችን ማሰባሰብ ተግባሩ ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡

ኮሚሽኑ በሚተዳደርበት አዋጅ 1265/2014 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ከመላ ሀገሪቱ የምክክሩ ዜጎች፣ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት ሃሳባችንን ያሰሙልናል የሚሏቸውን ተሳታፊዎች ከለዩ በኋላ በክልሎችና በፌዴራል ደረጃ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ እየተካሄደ መሆኑን ያስረዳሉ።

በመሆኑም የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ሀገራዊ መግባባት

ቁልፍ ሀገራዊ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# ዩኒማስ ኢንጂነሪንግ - የሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎች ተምሳሌት

**ሞገስ ጸጋዬ**

**ዜና ሐተታ**

መንግሥት የሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎች በጥራትና በብቃት አምርተው የሀገር ውስጥ ፍጆታን እንዲያሟሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችን ከማሻሻል ጀምሮ በርካታ እገዛዎችን እያደረገ ነው።

ከውጭ ለሚገቡ ምርቶች የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ መቀነስ፣ ወደ ውጭ የሚላከውን ደግሞ በመጨመር የውጭ ምንዛሪ ገቢን ማሳደግ በመንግሥት ከተያዙ ሀገራዊ እቅዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው።

በኢትዮጵያ ካሉ ሀገር በቀል ኢንዱስትሪዎች መካከል ኃይል ቆጣቢ መብራቶች፣ ብሬከሮች፣ ኤክስቴንሽን ሶኬቶች፣ ቮልቴጅ መቆጣጠሪያዎችና ሌሎችን የኤሌክትሪክ ውጤቶችን የሚያመርተው ዩኒማስ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተጠቃሽ ነው።

ዩኒማስ በ2005 ዓ.ም በመንግሥት የተመዘገበ ድርጅት ነው። ከውጭ ይገቡ የነበሩ በርካታ የኤሌክትሪክ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚገባውን የመተካት ሥራ እየሠራ ይገኛል። የዓመቱ ለኤሌክትሪክ ግዥ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ መቀነስ አስችሏል፡፡

የዩኒማስ ኢንጅነሪንግ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መሀመድ ሙዘይን እንደሚገልጹት፤ ዩኒማስ የተለያዩ የኤሌክትሪክ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመገጣጠም ለ10 ዓመታት የቤት ውስጥና የኢንዱስትሪ የመገልገያ እቃዎችን እያቀረበ ይገኛል። በዚህም ለ97 ቋሚና ለ22 ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር ችሏል፡፡

ወደፊት በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪያል ፓርክ የጀመረውን ማስፋፊያ ሥራ ሲጀምር 300 የሚደርሱ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ያነሳሉ፡፡

ምርቶች በኢትዮጵያ የደረጃዎች ባለስልጣን ባወጣው ደረጃ መሠረት እንደሚመረቱ ጠቅሰው፤ በሀገር ውስጥ ደረጃ ያልተቀመጠላቸውን ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ መሠረት እየተመረቱ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ጥሬ እቃዎች ቀደም ብለው የገቡ በመሆኑ ምርቶች ላይ የዋጋ ማሻሻያ አልተደረገም ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ወደፊትም ቢሆን የኅብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ ለገበያ ማቅረባችንን እንቀጥላለን ይላሉ፡፡

ድርጅቱ ወደ ሥራ ከገባ ጀምሮ በውጭ ምንዛሪ ይገቡ የነበሩ የኤሌክትሪክ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመሸፈን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ፤ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ ተችሏል ሲሉ ይገልጻሉ።

ዩኒማስ በቀጣይ ለጎረቤት ሀገሮች የኤሌክትሪክ ምርቶችን ለመላክ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አንስተው፤



አሁን ላይ ለኢንዱስትሪዎች፣ ለመኖሪያ ቤቶች፣ ለንግድ ተቋማት የሚሆኑ እቃዎችን ለሀገር ውስጥ ተጠቃሚዎች እያቀረበ እንደሚገኝ ያመላክታሉ።

የኤሌክትሪክ ምርቶች በሙሉ አቅሙ በሀገር ውስጥ ለማምረት 11 ሺህ 647 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪያል ፓርክ መረከቡንም ያስታውቃሉ። ምርቶችን በስፋትና በጥራት ወደ ገበያ ለማቅረብ ከታዋቂ ኩባንያዎች ማሽኖችን ለማስመጣት ቅድመ ዝግጁት ማጠናቀቁን ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማሰራጫና ማከፋፈያ ፕሬዚዳንት አቶ ወንዶሰን በላይ በበኩላቸው፤ ዩኒማስ ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ማስቀረት ችሏል፡፡ ለዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩን ይጠቁማሉ።

በጥራት ላይ የተመሠረተ አምራች ኢንዱስትሪ በመሆኑ ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። እንዲሁም ዩኒማስ የሚያመርታቸው የኤሌክትሪክ እቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እያቀረበ ነው ይላሉ።

በርካታ የኤሌክትሪክ እቃዎች ጥራታቸውን ሳይጠብቁ በገበያ ላይ ይገኛሉ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህም ለመንግሥትና ለኅብረተሰቡ ፈተና ደቅኗል፤ ኅብረተሰቡም ከፍተኛ ጉዳትን እያስተናገደ ነው፡፡ እንዲሁም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

ዩኒማስ ተደራሽነቱን ለማስፋት የጀመረው የማስፋፊያ ሥራ ተጠናክሮ እንዲሄድ፣ ጥራት ያላቸው ምርቶች ለሀገር ውስጥ ተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ለማድረግ መንግሥት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲሠራ ቦታ መስጠቱ የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ነው የተናገሩት።

ይህም በቀጣይ ለተለያዩ የኤሌክትሪክ ምርቶች የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ በከፍተኛ ሁኔታ ለማስቀረት እንደሚረዳ አንስተው፤ ወደፊት ከሀገር ውስጥ ፍጆታ በሻገር ወደ ውጭ ሀገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት እንደሚያግዝ ይገልጻሉ።

# የጥራት ተሸላሚው ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

**ነፃነት አለሙ**

በሀገራችን የመጀመሪያው የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ የሆነው ተግባረ-ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ1934 ዓ.ም እንደተቋቋመ ታሪኩ ይናገራል። በተቋቋመበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታትም “የረቂቅ ጥበብና የእጅ ብልሀት ሥራ ተማሪ ቤት” በመባል ይጠራ እንደነበር ከኮሌጁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ትምህርት ቤቱ የተቋቋመው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ስለነበር በቂ መምህራንን ከውጪ ሀገራት ለማስመጣት ተቸግሮ ነበር። ችግሩን ለመፍታትም ከወራሪው ጣሊያን ጋር መጥተው ከሽንፈት በኋላ ሰላማዊ ኑሮአቸውን እዚሁ ከቀጠሉ የጣሊያን ባለሙያዎች የተሻሉትን በመምረጥ በኮንትራት ቀጥሮ ያሠራ እንደነበር ሰነዶች ያስረዳሉ።

ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም በወቅቱ በተገኙ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች በመጠቀም ስልጠናውን እንደጀመረም መረጃው ይገልጻል፡፡

በኋላም በ1994 ዓ.ም እንደ ሀገር የሙያ ስልጠናና የቀለም ትምህርት ሲለያይ የአዲስ አበባ ተግባረ-ዕድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቀርፆ የትምህርት ዘርፎቹን በማሳደግ የኮሌጅነት ደረጃን መያዝ ችሏል፡፡

82 ዓመታትን ያስቆጠረው ኮሌጁ በመደበኛ፣



በማታውና በቅዳሜና እሁድ በተለያዩ ዘርፎች ከማሰልጠኑ ባሻገር በቅዳሜና እሁድ በኢትዮ ቻይና ኮሌጅ በዲግሪ ፕሮግራም ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡

ኮሌጁ ሰሞኑን የISO9001/2015 የጥራት ሥራ አመራር እውቅና ሰርተፊኬት አግኝቷል። የዕውቅና ሰርተፊኬቱ ተቋሙ አሠራሩን በማዘመን ብቁ የሰው ኃይልን በመቅረጽና ለኢንዱስትሪዎች አቅም በመገንባት ላሳየው ትጋት የተሰጠው መሆኑንም የጥራትና ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ መአዛ አበራ ይገልጻሉ።

በምዘና ሥርዓት ለማለፍ የአመራር ቁርጠኝነት እና የሥራ ትጋት የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን በመግለፅ ፤ለዚህም ኮሌጁ ያገኘው ሰርተፍኬት የአሠራር ሥርዓትን በማዘመን የደንበኞች እርካታን ለማሳደግ እንደሚረዳ ነው የተናገሩት።

በአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የውጤት ተኮር ስልጠናና ተቋማት አቅም ግንባታ ዘርፍ ኃላፊ አበራ ብሩ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ማፍራት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው። ለዚህም ኮሌጁ የጥራት አመራር ሥርዓት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ባለቤት መሆኑ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱ ይጨምራል።

የአዲስ አበባ ተግባረ-ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ዋና ዲን አቶ ግሩም ግርማ በበኩላቸው፤ ኮሌጁ 82 ዓመታትን ማስቆጠሩን አስታውሰው፤ በቀጣይ አመራሩና ሠራተኛው ዕድሜውን በሚመጥን ትጋት ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ኮሌጁ የደንበኞችን እርካታ መነሻ በማድረግ የ9001:2015 የጥራት አመራር ሥርዓት ለመተግበር ከታህሳስ 2015 ጀምሮ ወደ ተግባር በመግባት በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ነው ያስታወሱት።

ለጥራትና ተወዳዳሪነት ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን ማሟላት ወሳኝ መሆኑንና ኮሌጁ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማቅረብ፣ ለኢንተርፕራይዞች ድጋፍ በመስጠትና አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን በማጎልበት ለዚህ ዕውቅና መብቃቱን ነው ያስታወቁት።

# የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ ሥርዓት መመራቱ ቡና ላኪዎችን በዘላቂነት እንደሚጠቅም ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ ሥርዓት እንዲመራ መደረጉ ቡና ላኪዎችን በዘላቂነት እንደሚጠቅም የቡና ላኪዎች ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛት ወርቁ አስታወቁ፡፡

አቶ ግዛት ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ችግር የንግዱ ማህበረሰብ በሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እድገት የሚፈለገውን ተሳትፎ እንዳያደርግ አድርጎት ቆይቷል።

የንግድ ሰንሰለቱ በተለያዩ ችግሮች በመፈተኑ አስመጪና ላኪዎች መቸገራቸውን አስታውሰው፤ ሰሞኑን የተደረገው የውጭ ምንዛሬ ሥርዓት ማሻሻያ የንግድ ሥርዓቱን እንደሚያስተካክለው ገልጸዋል፡፡

መንግሥት በፋይናንስ ዘርፉ እየወሰዳቸው የሚገኙ ማሻሻያዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ ሥርዓት እንዲመራ መደረጉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት በተለይ ለቡና ላኪዎች ጉልህ ሚና ያበረክታል ብለዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በንግድ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ችግሮችን ይፈታል፡፡ የቡና ላኪዎች የተሻለ ገቢ ያገኙበታል፤ ቡናን በስፋት ወደ ውጭ ለመላክ ትልቅ እገዛ የሚሰጥ ማሻሻያ ነው፡፡

አሁን ላይ መደናገሮች በመኖራቸው አቅራቢዎች ያላቸውን ቡና ይዘዋል፤ የውጭ ሀገር ገዥዎችም የገንዘብ ልዩነት ስላለ ዋጋ ቀንሱ እያሉ ነው፡፡ ነገር ግን መሰል ችግሮች ጊዜያዊ ከመሆናቸውም በላይ ማሻሻያው ለቡና ላኪዎች ዘላቂ ጥቅም የሚሰጥ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ማሻሻያውን ተከትሎ ቡና ላኪዎች የመደራደር አቅማቸው ከፍ ይላል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ይህም በዘላቂነት ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፤ እንደ ሀገርም የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ያድጋል ብለዋል፡፡

ማሻሻያው በውስጡ በርካታ ነገሮችን ያቀፈ በመሆኑ የመንግሥት አካላት በጥንቃቄ ማየትና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ የዶላርና የብር የመገበያየት ሂደት የሚወሰነው በእቃዎቸ ዋጋ በመሆኑ የእቃዎችና የአገልግሎት ገበያው መፈተሽ እንዳለበት አመላክተዋል።

የእቃዎች መግዣና መሸጫ ካልተስተካከለ የዶላርና የብር ግብይት ሥርዓት የሚዛባ በመሆኑ መንግሥት ክትትል ማድረግ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ቡናን ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረገው ሂደት ውስጥ ያለው



አቶ ግዛት ወርቁ

የቡና የግብይት ሥርዓት ሊስተካከል ይገባል ብለዋል፡፡

ቡና አሁን ባለው የኢትዮጵያ የንግድ ሥርዓት ውስጥ 40 በመቶ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ወሳኝ ምርት ነው ያሉት አቶ ግዛት፤ ከፍተኛ የሥራ እድል የፈጠረ ዘርፍም በመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ቀደም ሲል የነበሩ መመሪያዎችን በአንድ መመሪያ ስር በማድረጉ ለቡና ላኪዎች ያለው ፋይዳ ትልቅ ዋጋ እንደሚኖረው አስረድተዋል።



# የተለያዩ ክልሎች ለአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሀ-ግብር ዝግጅት እያደረጉ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ለሚካሄደው የአንድ ጀንበር 600 ሚሊዮን ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን የተለያዩ ክልሎች አስታወቁ፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ማስረሻ በላቸው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአንድ ጀንበር 600 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል በክልሉ ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

በአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄው በክልሉ የሚገኙ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሰዎችን በማሳተፍ በሰባት ሺህ 560 ሄክታር መሬት ላይ 18 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ለአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ 23 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ችግኞችን የመለየት ሥራ ተሠርቷል ያሉት ኃላፊው፤ 18 ነጥብ አንድ ሚሊዮን የችግኝ መትከያ ጉድጓድ መዘጋጀቱን አንስተዋል። ለንቅናቄውም ስምንት መቶ 13 ቦታዎችን የለየ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ2016 ዓ.ም በክልሉ 400 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ ባለው ሥራ እስከ ነሐሴ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ280 ሚሊዮን ችግኝ በላይ ተተክሏል፤ ቀሪው እስከ መስከረም 30 ተተክሎ ይጠናቀቃል ያሉት አቶ ማስረሻ፤ ከሚተከለው 400 ሚሊዮን ችግኝ ውስጥ 60 በመቶ የሚሆኑት ለምግብነት የሚያገለግሉ ናቸው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበኸር ኃሊፍ በበኩላቸው፤ በአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ በአንድ መቶ 96 በተመረጡ ቦታዎች ላይ 500 ሺህ ሰዎችን በማሳተፍ 15 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ችግኞችን የማጓጓዝና ጉድጓድ የመቆፈር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ በክልሉ ለመትከል ከታቀደው 15 ሚሊዮን ችግኝ ውስጥ 60 በመቶ የሚሆኑት ለምግብነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ፤ 40 በመቶ የሚሆኑት ለአፈርና ውሃ ጥበቃ የሚያገለግሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በ2016 ዓ.ም በክልሉ 70 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ ባለው ሥራ እስከ ነሐሴ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 35 ሚሊዮን ችግኝ የመትከል ሥራ ተከናውኗል ያሉት አቶ ባበኸር፤ ቀሪውን ለመትከል ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ በአንድ ሺህ 226 ሄክታር መሬት ላይ 221 ሺህ 432 ሰዎች በማሳተፍ ሁለት ሚሊዮን 214 ሺህ 324 ችግኝ ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ነው ሲሉ በአፋር ክልል ግብርና ቢሮ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ምክትል ኃላፊ አቶ ኡሱማን መሐመድ ተናግረዋል፡፡

ንቅናቄውን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን የችግኝ ጉድጓድ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

በ2016 ዓ.ም በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በአምስት ሺህ 531 ሄክታር መሬት ላይ አስር ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለው ሥራ አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሚሆነውን የመትከል ሥራ እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ ተግባራዊ ለማድረግ ማህበረሰቡ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# “በምክክሩ ሂደት የራስን ሃሳብ አቅርቦ የሌላውን አካል አጀንዳ መስማት ይገባል”

**- የድሬዳዋ ከተማ ፖለቲካ ፓርቲዎች**

**ገመቹ ከድር**

ድሬዳዋ፡- በምክክሩ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ያልተሳተፉ አካላት የራስን ሃሳብ አቅርቦ የሌላውን መስማት የተሻለ አካሄድ መሆኑን ሊረዱ ይገባል ሲሉ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገለጹ፡፡

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የምክክሩ አጀንዳ ልየታ ምክክር መርሀ ግብር ተካሂዷል።

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አዲስ ትውልድ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት ወይዘሮ ስምረት ዘሪሁን ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚታገሉት የሕዝቡን ሰላምና ሕይወት ለማሻሻል እስከሆነ ድረስ በሩቁ ቆመው ከመወቃቀስ ይልቅ በተገኘው ዕድል ተጠቅመው ለሀገር የሚበጀውን አጀንዳ ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ እንደ ሀገር እየተካሄደ በሚገኘው የሀገራዊ ምክክር ሂደት ሁሉንም ያካተተና አሳታፊ በመሆኑ ሃሳብ አለኝ የሚል አካል ሁሉ አጀንዳውን ሊያስይዝ ይገባል።

እንደ ፓርቲያቸው ለሀገራዊ መግባባት ይበጃል ያሉትን አጀንዳዎች አስይዘው በምክክር መርሀ ግብሩ ሂደት መሳተፋቸውን ጠቁመው፤ መድረኩ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት ሃሳባቸውን የገለጹበት ሂደት እንደነበር አንስተዋል።

የምክክር ሂደቱ በዚህ ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ ከቀጠለ ለሀገር የሚበጁና ወደተሻለ ደረጃ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ ሃሳቦች እንደሚገኙበት ተስፋ አደርጋለሁ ያሉት ወይዘሮ ስምረት፤ እስከ አሁን በምክክር ስላልተጠቀምን ነው እንጂ በውይይት የማይፈቱ ነገሮች የሉም ሲሉ የሀገራዊ ምክክር ተሳትፎን አስፈላጊነት አብራርተዋል፡፡



ወይዘሮ ስምረት ዘሪሁን



ወይዘሮ እፍቱ አህመድ

በድሬዳዋ ከተማ ብልጽግና ፓርቲን ወክለው በአጀንዳ ልየታ መርሀ ግብር መድረክ ላይ የተሳተፉት ወይዘሮ እፍቱ አህመድ በበኩላቸው፤ በሀገራችን በምክክር ልዩነቶችን መፍታት ያልተለመደ ቢሆንም አሁን አንድ ብለን ጀምረናል፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሀገራችን ይመለከተኛል ያሉ ለሀገራቸው ይበጃል ያሉትን አጀንዳዎቻቸውን በማቅረብ በቡድን ተወያይተዋል ብለዋል፡፡

ሂደቱም ግልጽ፣ አካታች ፣ሁሉም በነጻነት የራሱን አጀንዳ ያቀረበበት እንደነበር አስታውሰው፤ ምክክሩ ያልተዋጠላቸው አንዳንድ አካላት ጠመንጃ ያነሱ ካለመሳተፍ ለሕዝባቸው ጥቅም ሲባል ከኮሚሽኑ ቀርበው ሃሳባቸውን አቅርበው የሌላውንም ቢሰሙ ይበጃል ሲሉ ተናግረዋል።

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢና የኢዜማ ፓርቲ አባል አቶ ዮናስ በትሩ፤ ስለሀገር ይመለከተኛል ያሉ በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ስምንት ፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአዘጋጀው ባለድርሻ አካላት አጀንዳ ልየታ መርሐ ግብር መሳተፋቸውን ጠቁመዋል።

ሁሉም በፓርቲ ደረጃ ለሀገራዊ መግባባት ግብዓት ይሆናል ብለው ያመኑበት አጀንዳዎች ይዘው በምክክር መድረኩ በመቅረብ ያለምንም ተፅእኖ እየተመከሩበት መሆኑን ገልጸዋል።

ምክክሩ እንደ አጀማመሩ ለሀገር የሚበጁ ገዥ ሃሳቦች በማመንጨት ለሀገራዊ መግባባት ግብዓት የሚሆኑ ተስፋ ሰጪ ጭብጦች እንደታዩበት አንስተው፤ ያልተሳተፉ አካላት ጠመንጃን እንደ መፍትሔ መውሰድ ውጤት እንደማያመጣ ካለፈው ታሪካችን ሊማሩ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እስካሁን በሂደቱ ያልተሳተፉ አካላት ወደምክክሩ መጥተው ሃሳባቸውን በማቅረብ የሌላውንም መስማትና ለሀገራዊ ዕድገት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

# ለዋጋ ንረቱ መፍትሔ የሆኑት የገበያ ማዕከላት

**መስከረም ሰይፉ**

**ዜና ሐተታ**

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በገበያ ላይ ሕገወጥ የምርቶች ዋጋ ጭማሪ መስተዋሉንና የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮም ችግሩን ለመግታት የተለያዩ ርምጃዎች እየወሰደ ይገኛል፡፡

የዋጋ ጭማሪ ከተስተዋለባቸው መካከል አንዱ የአትክልት ገበያ ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ የአትክልት ገበያው ምን ይመስላል? ዋጋውን ለማረጋጋትስ ምን እየተሠራ ነው ሲል ሸማቾችንና የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮን አነጋግሯል፡፡

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳባቸውን የሰጡት በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ቦታው ኮተቤ 02 አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ማርታ አያሌው፤ የአትክልት ገበያው ከአንድ ወር በፊት ከነበረበት ዋጋ አንጻር ጭማሪ ማሳየቱን ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ሽንኩርትም ሆነ ሌሎች አትክልቶች ላይ የተወሰነ የዋጋ ለውጥ ስለሚያገኙ በእሁድ ገበያ ይገዙ እንደነበር አስታውሰው፤ በግል ምክንያት ያንን ማድረግ ባለመቻላቸው ከመደበኛው ገበያ አንድ ኪሎ ሽንኩርት በ 90 ብር መሸመታቸውን ነው የተናገሩት፡፡

ከሽንኩርት በተጨማሪ ቲማቲም በኪሎ በ70 ብር መሸመታቸውን አንስተው፤ ቲማቲም በቅርቡ በ25 ከገዙ በኋላም 40 ብር ሸምተው እንደነበር ነው ያስታወሱት።

በገበያው ላይ እንደየደረጃው በቂ ምርት ቢኖርም ከሽንኩርትና ቲማቲም በተጨማሪ ሌሎች የአትክልት ዋጋ ላይ የተወሰነ ጭማሪ ማየታቸውን ይጠቁማሉ።

በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ጋርመንት አካባቢ የሚኖሩት ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ የሺ ገብረወልድ በበኩላቸው፤ በመደበኛው ገበያ ላይ ሽንኩርት አንድ ኪሎ 85 ብር እየተጠራበት በመሆኑ ወደላፍቶ የአትክልት ገበያ ማእከል በማቅናት አንድ ኪሎ ሽንኩርት በ65 ብር መሸመታቸውን ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ የሺ በአትክልት ማእከሉ ከሌሎች መደበኛ አትክልት ገበያዎች አንጻር ከሽንኩርት በተጨማሪ ሌሎች የአትክልት ምርቶች ላይ ቅናሽ መኖሩን ጠቅሰው፤



በማእከሉም ቲማቲም ከ25 ብር ጀምሮ መኖሩንና እርሳቸው ቆንጆ የሚባለውን ቲማቲም አንድ ኪሎ በ 30 ብር ፣ ድንች በ 23 ብር መሸማተቸውን ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የዋጋ ጭማሪውን አስመልክቶ ያነጋገራቸውን አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ሰውነት አየለ፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ጋር ተያይዞ በአትክልት ገበያው ላይ የተወሰነ የዋጋ መወደድ መስተዋሉን ይናገራሉ።

ቢሮው ያለአግባብ የሆነ ዋጋ ጭማሪን ለመከላከልና በከተማዋ የምርት እጥረት እንዳያጋጥም ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ምርቶችን ወደ ከተማዋ የማስገባት ሥራ ተሠርቷል ይላሉ። በተጨማሪም በላፍቶ፣ በኮልፌ፣ በአቃቂና በለሚኩራ የግብርና ምርቶች የገበያ ማእከላት አምራቾች ራሳቸው ምርቶችን የሚያቀርቡበት ሁኔታ መፈጠሩን ይጠቁማሉ፡፡

በገበያ ማእከላቱ በርካታ አቅራቢዎች መቀላቀላቸውን ገልጸው፤ ቢሮውም በሳምንት ሦስት ጊዜ ዋጋ እየተመነላቸው መሆኑንና በአሁኑ ጊዜም በነዚህ የገበያ ማእከላት ሽንኩርት ከ 45 ብር ጀምሮ እየተሸጠ መሆኑን ይገልጻሉ።

አቶ ሰውነት በመደበኛው ገበያ ምርቶቹ በበለጠ ዋጋ እየተሸጠ በመሆኑ አንዳንድ ነጋዴዎች የሚሰጠው ዋጋ አያዋጣንም እያሉ ምርቶቻቸውን በሌላ ቦታ እየሸጡ መሆኑንና ይሁን እንጂ በማእከላቱ በቂ የሚባል ምርት መኖሩን ይናገራሉ፡፡

ምንም አይነት የምርት እጥረት አለመኖሩን በመጥቀስ፤ ኅብረተሰቡ የግብርና ምርቶችን ከነዚህ ማዕከላት እንዲገዛ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ቢሮው በአትክልት ተራዎች አንድ ምርት ብቻውን መግዛት አይቻልም አልያም በችርቻሮ አይሸጥም የሚባሉ ሕገወጥ ድርጊቶች በመኖራቸው ርምጃ መውሰዱን አንስተው፤ ኅብረተሰቡ እንደነዚህ አይነት ሕገወጥ ድርጊቶች ሲያጋጥሙት ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአዲስ አበባን ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥሉ!

ከተመሰረተች ከ130 ዓመት በላይ የሆናት አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ፤ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የአፍሪካ መዲና እና የተለያዩ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ ናት። ከ90 በላይ ኤምባሲዎችን በማቀፍም በዓለም ላይ ካሉት ጥቂት የዲፕሎማቲክ ማዕከል ከሆኑት ከተሞች ውስጥ ግንባር ቀደምም ናት፡፡

ሆኖም ይህቺ የዲፕሎማሲ መናኸሪያ ስሟና ግብሯ ለዘመናት ተራርቆ ቆይቷል፡፡ ከተማዋ ከምስረታዋ ጀምሮ በዘመናዊ ማስተር ፕላን የተቀረቀረች ባለመሆኗ እና ለዘመናትም አስታዋሽ አጥታ በመቆየቷ በእርጅና ብዛት ለመፍረስ ተቃርባ ነበር፡፡የመሰረተ ልማት ዝርጋታዋም ሆነ አረንጓዴ ሽፋኗ አንድ ከተማ ሊያሟላ ከሚገባው ዝቅተኛ መስፈርት በእጅጉ የራቀ ሆኖ ቆይቷል፡፡ አዲስ አበባን እንደ ገጠር ማስተዳደር በሚል የተሳሳተ መርህ መሠረትም ከተማዋ የኋሊት ስትጓዝም ቆይታለች፡፡

ሆኖም የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎ ከተማዋ ባገኘችው ትኩረት አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ አበባ የመሆን እድል አግኝታለች፡፡ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብሎም አፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ የሆኑ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑባት ነው፡፡ከተማዋ በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት የሚያበቋት የተለያዩ መሠረተ ልማቶችና የመዝናኛ ስፍራዎች በስፋት እየተከናወኑባት ይገኛሉ፡፡

የአዲስ አበባን ገጽታ የሚቀይሩ እና የቱሪስት ፍሰት የሚያሳድጉ ሥራዎችንም በመሥራት ከኢትዮጵያ አልፋ የአፍሪካ መዲና የሆነችው ከተማ በጎብኚዎች ተመራጭ ሀገር እንድትሆን የተሠራውም ሥራ የብዙዎችን ቀልብ የገዛ ነው፡፡ በገበታ ለሸገር ፕሮጀክት የአንድነት፣ የወንድማማችነትና የእንጦጦ ፓርኮች ከአዲስ አበባ አልፈው የሀገር ኩራት ለመሆን በቅተዋል። በአዲስ አበባ የተሠሩት አመርቂ ሥራዎችም ኮይሻን፣ ጎርጎራንና ወንጪን ለመሳሰሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች መነሻ ለመሆን በቅተዋል፡፡

በቅርቡ ደግሞ የአዲስ አበባን ገጽታ ከመሰረቱ የሚለውጥ ግዙፍ የኮሪደር ልማት በአምስት አቅጣጫዎች መተግበር ጀምሮ ወደ መገባደዱ ተቃርቧል፡፡ የኮሪደር ልማቱ የተጎሳቆለውን አዲስ አበባ ገጽታ ለመቀየር ከማስቻሉም በላይ አዲስ አበባ ከአቻ የዓለም ከተሞች ጋር መሳ ለመሳ እንድትቆምና የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ማዕከል እንድትሆን በር የሚከፍት ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም በባለሀብቱና በመንግሥት ቅንጅት የከተማዋን ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በዋነኛነት በቻይና እና በተባበሩት አረብ ኤምሬት መንግሥታትና ባለሀብቶች ትብብር የሚሠሩ ጉልህ የልማት ሥራዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከእነዚህ ጉልህ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ሰሞኑን የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለት የአዲስ ቱሞሮ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ነው፡፡ በ35 ሄክታር መሬት ላይ ከቻይናው “ሲሲሲሲ” ጋር በመተባበር የሚገነባው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በከተማ ውስጥ አዲስ ከተማን የመገንባት ያህል የሆነው ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት ከመሠረቱ የአዲስ አበባን ገጽታ የመቀየር አቅም እንዳለው ታምኖበታል፡፡ የኢኮኖሚ ዞኑ በውስጡ ትላልቅ ሞሎችን፣ የመኖሪያ አፓርትመንቶችን፣ ቢሮዎችን፣ የትምህርት እና የጤና ተቋማትን እንዲሁም ሰፋፊ መዝናኛዎችንና የውሃ አካላትን እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከላትን ያካተተ ነው፡፡

አዲሱ የኢኮኖሚ ዞን ለመዲናዋ አዲስ ገፅታ የሚያላብስ፣ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቷን የሚያጎላ፣ ተጨማሪ የውበት ምንጭ የሚሆን፣ ለነዋሪዎች ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጥር እና ንግድን የሚያሳልጥ ትልቅ ዓለም አቀፍ የግብይት ማዕከል እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና አዲስ ለማድረግና አልፎ ተርፎም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ያረጋገጠች ከተማ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተስፋ ሰጪ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ገጽታ መለወጥም የአፍሪካ መዲናነቷን ለማጽናት ከማስቻሉም ባሻገር ከተማዋን የቱሪዝምና ኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መነቃቃት የማይተካ ሚና እንድትጫወት ያደርጋታል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ከናይል ትብብር እስከ ባህር በር

እስማኤል አረቦ

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የመጀመሪያው ትኩረት የጎረቤት ሀገራት በመሆናቸው ኢትዮጵያ ከየትኛውም ዓለም አቀፋዊም ሆነ አህጉራዊ ጉዳዮች በበለጠ ለጎረቤት ሀገራት የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ትሰጣለች፡፡ ይህንኑ መነሻ በማድረግም ግጭት እና ሁከት ውስጥ የሚገኙትን ሶማሊያ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በመሪዎች መካከል ተደጋጋሚ ውይይት እንዲደረግ ኃላፊነትን በመውሰድና አልፎ ተርፎም የሰላም አስከባሪ በመላክ ሀገራቱ አንጻራዊ ሰላም እንዲኖራቸው አበክራ በመሥራት ላይ ትገኛለች፡፡

ሶማሊያ መንግሥት አልባ ሆና ለዓመታት ቆይታለች። ኢትዮጵያ ባደረገችው ጥረት እኤአ ከ2008 ጀምሮ ሶማሊያ መንግሥት መስርታ አንጻራዊ ሰላም አግኝታ ቆይታለች፡፡ ለሶማሊያ መረጋጋትና የሶማሊያን ሕዝብ ለመታደግ ሲባልም ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን አጥታለች፡፡ በተመሳሳይም ሱዳን ግጭት ውስጥ በገባችበት ወቅት ከሕዝቡ ጎን በመቆም ሱዳን ወደ ተሻለ ሰላምና መረጋጋት እንድትመጣ ኢትዮጵያ የበኩሏን ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡

ከአንድ ወር በፊትም በግጭት አዙሪት ውስጥ የምትገኘውን ይህችን ሀገር ወደ ሰላሟ እንድትመለስ ማንም መሪ ባላደረገው መልኩ ፖርት ሱዳን ድረስ በመሄድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከሱዳን ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ አል ቡርሃን ጋር ተወያይተው ተመልሰዋል፡፡ ውይይታቸውን ካጠናቀቁ በኋላም “የወንድም ሱዳን ሕዝብ ችግር የኛም ችግር፣ሰላማቸውም ሰላማችን በመሆኑ ለሱዳን ሕዝብ እፎይታ እና የብልፅግና ጉዞ ዛሬም እንደ ትናንቱ ከልብ እንሠራለን።” ሲሉ ገልጸዋል።

አዲሲቷ ሀገር ደቡብ ሱዳንም እንደ ሀገር እንድትቆም ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሚና ከመጫወቷም ባሻገር በሀገሪቱ የነበረው የእርስ በእርስ ግጭት እንዲያባራና አንጻራዊ ሰላም እንዲረጋገጥ የማይተካ ሚና ተጫውታለች፡፡ በጎረቤት ሀገራት የሚታየው ግጭትና ጦርነት እንዲያበቃ ከመሥራት ጎን ለጎንም የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በልማት እንዲተሳሰሩ በማድረግ ረገድም የኢትዮጵያ ሚና የጎላ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በተለይም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በየዓመቱ በበርካታ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን በመትከል በቀጣናው የሚታየውን ድርቅ በዘላቂነት ለመቋቋም አበክራ በመሥራት ላይ ትገኛለች፡፡ የቀጣናውን ሀገራት ልማት በማቀራረብ ረገድ እየተጫወተች ያለው ሚና በአካባቢ ጥበቃ ብቻ የተገታ አይደለም፡፡በተለይም ከዓባይ ግድብና ከጊቤ ሦስት ግድቦች የሚነጭ ኃይልን ለጎረቤት ሀገራት በተመጣጣኝ ዋጋ በማዳረስ ቀጣናው በኃይል እንዲተሳሰር በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የኢትዮጵያውያን የዘመናት ጥያቄ የሆነው የዓባይ ወንዝን በትብብር የማልማት ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ አበክራ ስትሠራ ቆይታለች፡፡ ሰሞኑንም ደቡብ ሱዳን የናይል የትብብር ማዕቀፍን ማጽደቋም የዚሁ ጥረት አንዱ ማሳያ ነው፡፡የተፋሰሱ ሀገር የወሰደችውን ርምጃ፣ የጎረቤቷ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ “ታሪካዊ” ሲሉ አድንቀዋል፡፡

በሌላ መጠሪያው “የኢንቴቤ ስምምነት” እየተባለ የሚታወቀው የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት፣ በደቡብ ሱዳን መጽደቁ፣ ስምምነቱ በተፋሰሱ ሀገራት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን በቂ ድጋፍ የሚያስገኝ ነው፡፡ ደቡብ ሱዳን ስድስተኛ ሀገር ሆና የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱን መፈረሟ፣ ስምምነቱ “ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝና ወደ ተግባር እንዲሸጋገር የሚያስችል ነው፡፡

አሥራ አንዱም የተፋሰሱ ሀገራት የሚጋሩትን የናይል ወንዝ፣ “ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ለግብጽ እና ለሱዳን ብቻ ያከፋፍላሉ፤” በሚል የሚተቹትን የቅኝ ግዛት ስምምነቶች የሚሽርም እርምጃ ነው፡፡ ይህንን ኢ ፍትሐዊ አካሄድ ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትታገለው የቆየችው ነው። ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በደቡብ ሱዳን መጽደቁ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ነው፤” ሲሉ በማህበራዊ የትስስር ገጾቻቸው ያወደሱት፡፡

የናይል ወንዝን በጋራ ለማልማት ወደ ሚያስችል ስምምነት ለማምጣት 11 ዓመታት ወስዷል፡፡ ለ11 ዓመታት ከዘለቀ ውይይት በኋላ፣ በ2002 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ 2010) ግንቦት ወር ላይ በኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ዑጋንዳ፣ ሩዋንዳ እና ኬንያ ሲፈረም፣ ብሩንዲ በቀጣዩ ዓመት ስድስተኛ ሀገር ሆና ፈርማለች፡፡ በቅርቡ ደግሞ ደቡብ ሱዳን ስድስተኛዋ የስምምነቱ አጽዳቂ ሀገር ሆናለች፡፡

በዓለም ላይ ወደ 276 የሚጠጉ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አሉ። ይህንን 145 የሚሆኑ ሀገራት ይጋራሉ። አንዳንድ ሀገራት ወንዞቹን የሚመለከት ሕግ አላቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የጋራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ የላቸውም። ነገር ግን ሕጉ ያላቸው ሀገራት ውሃን ዘላቂና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ይገኛሉ።

የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት የዓባይን ውሃ በጋራ፣ በእኩልነትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ውሃውን መጠቀምና አብሮ መንከባከብ የሚያካትትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የሚተዳደሩባቸውን መርሆችን ጭምር ያካተተ ማዕቀፍ ነው። ይህም በአሥራ አንድ ሀገራት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።

ጉዳዩን የኢትዮጵያ መንግሥት የቅርብ ክትትል ያደረገበት በመሆኑ የተሳካ እየሆነ መጥቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሥራ ባልደረቦቻቸው የተለያዩ ሀገራት መሪዎችን በሚያገኙበት አጋጣሚ የውሃ ሀብትን በጋራ ማልማትና መጠቀም የሚቻልባቸውን መንገዶች ያነሳሉ። ይህም የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲ ሥራ ማሳያ ነው።

በየዓመቱ የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ መድረክ ላይ የውሃ ሚኒስትሮች ይሰበሰባሉ። በዚህም ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ሀገራት የውሃ ሀብቶችን በትብብር ማልማትና ማስተዳደር የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ እና ለጋራ ተጠቃሚነት ኢትዮጵያ ሁሌም ቅድሚያ እንደምትሰጥ ተናግራለች። ይህም ደቡብ ሱዳንን የመሳሰሉ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉን እንዲፈርሙና የናይል ትብብር ኮሚሽን ከስድስት ወራት በኋላ እንዲቋቋምና ተቋም ሆኖ እንዲወጣ በር የሚከፍት ነው፡፡

እንደ ናይል ትብብር ማዕቀፉ ሁሉ የባህር በር ባለቤት ለመሆንም ዲፕሎማሲ ጥረቶች ቀጥለዋል፡፡ በቱርክ አደራዳሪነትም ለሁለት ጊዜያት ያህል በአንካራ ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ያደረጉት ድርድርና በቀጣይም የሚያደርጉት ውይይት የዚሁ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማሳያ ነው፡፡

የባህር በር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ይህን መነሻ በማድረግ የባህር በርና ወደብ አማራጮችን ለማግኘት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሰላማዊ በሆነ መልኩ ጥያቄውን በማቅረብ ላይ ትገኛለች፡፡ ሆኖም ይህንን ጥያቄ ቀድማ የተቀበለችው ሶማሌላንድ ብቻ ነች፡፡ ዋናዋ ሶማሊያም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ የመሆን ዕድል ቢኖራትም ጥያቄውን ስትገፋ ቆይታለች፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በፓርላማ ተገኝተው እንዳሉት፤ «የሶማሊያ መንግሥት በአንድ ሰዓት በረራ እና በአንድ ሰዓት ውይይት ይህን ነገር መልክ ማስያዝ ይችላል። በጣም ቀላል ነገር ነው። ምክንያቱም ከሶማሌ መንግሥት ጋር ምንም ጸብ የለንም፡፡

እኛ ለመነጋገር ዝግጁ ነን። ሶማሊያ እንድትጎዳ፣ እንድትፈራርስም ፣ እንድትበተንም የሚፈልግ መንግሥት አይደለም፡፡ ቢሆን ኖሮ ልጆቹን ልኮ እንዲሞቱ አያደርግም ነበር ።የኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ የባህር በር ጥያቄ ነው። ይሄ ሕጋዊ ጥያቄ ነው ። ይሄን በሰላማዊ እና በንግግር መልኩ እንደማገኘውም ኮሚዲቲ / ሸቀጥ ለመቀበል ኢትዮጵያ ዝግጁ ነች።» ሲሉ ኢትዮጵያ ከየትኛውም ሀገር ጋር ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን በመጠቀም ብቻ የባህር በር ጥያቄዋ መልስ እንዲያገኝ እንደምትሰራ ተናግረዋል፡፡

ይህ ሀገሪቱ በሰላማዊ መንገድ የባህር በር የማግኘት ፍላጎት፤ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እውቅና እያገኘ የመጣ ፤ ለተግባራዊነቱ የሀገራት አዎንታዊ ድጋፍ እየተቸረው ይገኛል ።በመጪዎቹ ጊዜያትም ጥረቶቹ ፍሬ አፍርተው ፤ ሀገሪቱ የአዲስ የባህር በር ትርክት ባለቤት መሆን እንደምትችል ተስፋችን ጠንካራ ነው ።

ዜና

# የናይል ተፋሰስ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

አቶ ፈቅ አህመድ፤ በቅርቡ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ማጽደቋን ተከትሎ ዓለም አቀፍ ስምምነት ይሆናል ይላሉ።

እስከአሁን ባለው መረጃ ስምምነቱን የፈረሙ ስድስቱም ሀገራት ያጸደቁበትን ሰነድ ለአፍሪካ ኅብረት ማስገባታቸውን ጠቁመው፤ ከዚህ በኋላ የአፍሪካ ኅብረት በ60 ቀናት ውስጥ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት ትችላላችሁ ብሎ ያጸደቁትን ሀገራት ያሳውቃል ሲሉ ሂደቱን ያስረዳሉ።

ከዚያም ሀገራቱ ወደ ትግበራ እንደሚገቡና የመጀመሪያ ሥራቸው የናይል ተፋሰስ ኮሚሽንን ማቋቋም እንደሚሆን የሚናገሩት አቶ ፈቅ፤ የኮሚሽኑ ሥራ ስምምነቱን መተግበር እንደሚሆንና በተፋሰሱ ውስጥ የውሃ አስተዳደርን፣ አጠቃቀምን እና ጥበቃን በተመለከተ በተለይም ፈርመው ባጸደቁ ሀገራት ዘንድ ገዢ ሰነድ እንደሚሆን ያመላክታሉ።

ስምምነቱ ዓለም አቀፍ መርሆችን፣ ሕጎችን፣ ሂደቶችንና ተሞክሮዎችን ያካተተ እንዲሁም ሁሉንም ሀገራት ያሳተፈ ስለሚሆን የቅኝ ግዛት ዘመን ውሎችን የሚቀለብስ፤ በተፋሰሱ ውስጥ እውቅና ያለውና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኝ ሰነድ ይሆናል ሲሉም ያክላሉ።

በስምምነቱ መሠረት ኮሚሽኑ ሲቋቋም አሁን ያለውን የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ እንደሚወርስ የሚጠቁሙት የውሃ ሀብት አስተዳደር አማካሪው፤ ከዚህ ቀደም ኮሚሽኑ ምን መሥራት አለበት በሚል የተጠና ጥናት አለ፡፡ ጥናቱ በተወሰነ ደረጃ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ መከለስ አለበት ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ በቅድሚያ የተጠናውን ጥናት ተመልክታ ኮሚሽኑ በምን መልኩ ቢመሰረት፣ ምን አይነት ተግባርና ኃላፊነት ቢኖረው እና እንዴት ያሉ አጀንዳዎችን ቢያስተናግድ የተፋሰሱ ሀገራት በሙሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ በሚለው ላይ ከወዲሁ መሥራት አለባት ሲሉ ይመክራሉ፡፡

አያይዘውም፤ የስምምነቱ አንኳር ድንጋጌዎች ፍትሐዊና ምክንያታዊ አጠቃቀምን በተፋሰሱ ውስጥ ማስፈን እና በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ ጉልህ ጉዳት ያለማድረስ የሚሉ መሆናቸውን አንስተው፤ ሁለቱ መሠረታዊ ገዢ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ ጉልህ ጉዳት አለማድረስ የሚለው ሁለተኛው ጉዳይ ወደ ተግባር የሚመጣው፣ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠቀሰውን ፍትሐዊና ምክንያታዊ አጠቃቀምን በተፋሰሱ ውስጥ ማስፈን ካልተቻለ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የኮሚሽኑ ዋነኛ ሥራ በተፋሰሱ ፍትሐዊና ምክንያታዊ አጠቃቀምን ማስፈን ነው የሚሉት አቶ ፈቅ፤ በተጨማሪም በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ትብብር፣ የመረጃ መለዋወጥ እና ለተፋሰሱ የሚደረግ የጋራ ጥበቃ እንዲኖር የሚያደርጉ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ በዋነኝነት ግን ውሃውን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችሉ ዋና ዋና ውሳኔዎች የሚተላለፉበት ትልቅ መድረክ እንደሚሆን ያመላክታሉ።

ኢትዮጵያ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅና በተፋሰሱ ውስጥ ያላትን ሚና በተጠናከረ መልኩ ታስቀጥላለች የሚል እምነት እንዳላቸውም ይገልጻሉ፡፡

የውሃ ሳይንስ መሐንዲሱ ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ በበኩላቸው፤ የኮሚሽኑ መቋቋም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የተፋሰሱ ሀገራት፣ ለግብጽና ሱዳን ጭምር ዕድል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል ይላሉ፡፡ ምክንያታቸውን ሲያነሱም ተፋሰሱ ውስጥ በትብብር ውሃውን በስምምነት መጠቀም ከተቻለ የሁሉም ተጠቃሚነት ስለሚረጋገጥ ሁለንተናዊ ትስስራቸው እንዲጠነክር በማድረግ በቀጣናው ኢኮኖሚያዊ መሻሻልና መረጋጋት እንዲኖር ያደርጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደሚናገሩት፤ ናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭን ኢትዮጵያ ናት ያቋቋመችው ማለት ይቻላል፡፡ በየዓመቱ የተደረጉትን ስብሰባዎች ብንመለከት ኢትዮጵያ የሌሎችንም ሀገሮች ድርሻ ደርባ ደራርባ ስትወጣ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ወደ ድርድር ገብተን ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ካላበጀን የምናደርገው ትግል ሁሉ ዋጋ አይኖረውም በሚል ውትወታ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራትን አስተባብራ የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ እንዲቋቋም አድርጋለች፡፡ ከዛ በፊት የነበሩት የይስሙላ የትብብር ሥራዎች የግብጽና የሱዳንን ጥቅም ለማስጠበቅና ሌሎች ሀገራትን ለማዘናጋት የታቀዱ ነበሩ፡፡

ኢኒሼቲቩ በአብዛኛው መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን የሚገልጹት የውሃ መሐንዲሱ፤ ወደ ኮሚሽንነት ሲሸጋገር ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን የማድረግ አቅም ይኖረዋል። የዲፕሎማሲያዊ አቅምን ለመጨመር ያግዛል፡፡ በአጠቃላይ በናይል ተፋሰስ ሀገራት ዘንድ በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በአካባቢ ጥበቃና በተለያዩ ጉዳዮች እንደ አንድ አካባቢ ሀገራት መተባበር በውሃ ላይ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚፈጠረውን ጫና ይቀንሳል ይላሉ፡፡

ብቻዬን ልጠቀም ከሚል እሳቤ የተነሳ ከግብጽ የሚነሳውን ጥያቄ በተመለከተ በቂ አጸፋዊ ምላሽ ለመስጠት የኮሚሽኑ መቋቋም ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ያነሳሉ። የተቀሩት የተፋሰሱ አባል ሀገራት ድርሻ ትንሽ ቢሆንም ሉዓላዊ ሀገራት ናቸውና ሲሰባሰቡ ትልቅ የተሰሚነት አቅም እንደሚፈጥሩም ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ አሁን እያገባደደች ባለችው ግድብ ጭምር ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት ደግሞ በታሳቢነት በያዟቸው ሥራዎች ‘ነግ በእኔ’ ብለው በማሰብ ከወዲሁ ከስጋት ነጻ የሚያደርጋቸው አሠራር እንዲፈጠር አብረው መታገል አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ድርጅት ስለሚያስፈልግ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን እውን መሆን ትልቅ ፋይዳ አለው ይላሉ።

ሱዳንና ግብጽ የኮሚሽኑን እውን መሆን እንዴት እንደሚመለከቱት ሲያብራሩ፤ ሱዳን እ.ኤ.አ በ1959 ስምምነት የተመደበልኝ ውሃ አናሳ ነው በሚል ደስተኛ አይደለችም፡፡ ስለዚህ ሱዳን ከተረጋጋችና ጠንካራ መንግሥት መመስረት ከቻለች አዲሱ ስምምነት ወደዓለም አቀፍ ሕግነት ሲሸጋገር የመቀላቀል ፍላጎት አላት የሚሉት የውሃ መሐንዲሱ፤ ፕሬዚዳንት ኡመር አልበሽር ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ይህን ፍላጎታቸውን በግልጽ መናገራቸውን በአስረጂነት ይጠቅሳሉ፡፡

የግብጾች ወደ ኮሚሽኑ የመምጣት ነገር የናይልን ጉዳይ ሕገ መንግሥታዊ በማድረጋቸው ትንሽ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው የሚጠቁሙት ፕሮፌሰር አድማሱ፤ ስምምነቱን ከተቀበሉ ከሕገ መንግሥታቸው ጋር ይጋጭባቸዋል፡፡ ነገር ግን እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም፡፡ ሀገራት የስምምነቱ አካል እንዳይሆኑ ይሠራሉ፡፡ በቅርቡ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ካጸደቀች በኋላ ያጸደቀችበትን ሰነድ ለአፍሪካ ኅብረት እንዳታስገባ ትልቅ ሙከራ ሲያደርጉ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካላቸውም ይላሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ በታዛቢነት እንሳተፍ የሚል ጥያቄ ማቅረብ መሆኑን ጠቁመው፤ ታዛቢ ነን ብለው ውስጥ ገብተው በውሳኔዎች ላይ ጫና ለመፍጠር የሚሞክሩ ይሆናል፡፡ ያን ደግሞ የኮሚሽኑ አባል ሀገራት መፍቀድ የለባቸውም፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን ቢመራቸውም መድረኩ ትላልቅ ውሳኔ የሚወሰንበት በመሆኑ ስምምነቱን ለመቀላቀል እንደሚገደዱ ይገመታል ሲሉ አስተያየታቸውን ይቋጫሉ።

# ቁልፍ ሀገራዊ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ሊደረግባቸው ያስፈልጋል የሚሏቸውን እጅግ መሠረታዊ ጉዳዮች በሕዝባዊ ውይይት የሚሰበስቡበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ይህም በኢኮኖሚ፣ማህበራዊ እንዲሁም ከጸጥታ አንጻር የሚነሱ ሃሳቦችና ጥያቄዎች ለማሰባሰብ እንደሚረዳ ያነሳሉ።

የሚሰበሰቡት አጀንዳዎችም ኢትዮጵያውያን በመካከላቸው ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችና መፍትሔዎች ዙሪያ በንግግርና ውይይት መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚያመላክት ግብአት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ኮሚሽኑ ከሚከተላቸው መርሆዎች ውስጥ አካታችነትና አሳታፊነት ዋነኞቹ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በዚህም የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላትን በማካተት እየተሠራ መሆኑን ነው ያስረዱት። እነዚህ ተወካዮችም ከወረዳ ጀምሮ የሚገኙ ሴቶች፣ወጣቶች፣አካል ጉዳተኞች፣ተጽእኖ ፈጣሪዎች ፣መምህራን ፣የመንግሥት ሠራተኞች፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የመሳሰሉት ከተለያዩ ቦታዎች የተመረጡ ተወካዮች ሲሆኑ፤ ይህም እንደ ሀገር ለሚደረገው የምክክር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ነው ይላሉ።

በየዘርፋቸው ብሎም በክልላቸው ያጋጠሟቸው መሠረታዊና መፍትሔ የሚፈልጉ እንዲሁም በሀገር ደረጃ የሚታዩ እጅግ መሠረታዊ ችግሮችን ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የመለየት ሥራ የሚሠራበት ሂደት በመሆኑ አሳታፊነቱን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ኮሚሽነሩ እንደሚገልጹት፤ በአጀንዳ ማሰባሰብ ላይ ሁሉምን አሳታፊ ማድረጉም በየዘርፉ የሚያነሱትን ጥያቄዎችና አጀንዳዎች ለማካተት የጋራ ሀገራዊ መፍትሔ ለመስጠት ያስችላል። የተሰበሰቡት አጀንዳዎች ለሀገራዊ ምክክር ቀርበው ሰላምና ደህንነቷ የተጠበቀ ሀገር ለመገንባት የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦች የሚለዩበት ወሳኝ የምክክር ምእራፍ ነው፡፡

በቀጣይም ኮሚሽኑ ከቀረቡት አጀንዳዎች ውስጥ እጅግ መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮችን በመለየት ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክር ቤት የሚቀርብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በመጨረሻም ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ ይጠራል፡፡ በዚህም ቁጥራቸው ከ2ሺህ 500 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ይሳተፉበታል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጉባኤው የምክክር ሂደት በማድረግ ለጉዳዩ የመፍትሔ ሃሳቦችን ያቀርባሉ ሲሉ ሂደቱን ያብራራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአማካሪ ኮሚቴ አባል የሆኑት ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ በበኩላቸው፤ ለምክክሩ የሚሰበሰቡ አጀንዳዎች በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ችግሮችና መፍትሔ ላይ እንዲሁም ወደ ሰላም ለመግባት እንደሀገር ምን ይጠበቃል የሚሉ ወሳኝ ጉዳዮችና ጥያቄዎች የሚወጡበት ነው ይላሉ።

በሀገራዊ ምክክር ቀርበው ውይይት ሊደረግባቸው ይገባቸዋል የሚሉትን መሠረታዊ ችግሮችና ሃሳቦች በመለየት ያወጣሉ፡፡ ከዚህም በኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት መፈታት ያልቻሉ አጀንዳዎች ከተለዩ በኋላ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የሚለዩ ይሆናል ሲሉ ያመላክታሉ።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደሚገልጹት፤ በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ ላይ ሴቶች፣ወጣቶች፣በተለያዩ የሥራ መስክ የተሠማሩ ባለሙያዎች ፣የሃይማኖት አባቶች፣ተጽእኖ ፈጣሪዎች፣አካል ጉዳተኞች ፣በተለያየ መልኩ የተገለሉ የማህበረሰብ አካላትን ጨምሮ እስከ ላይኛው እርከን ያካተተ ሲሆን፤ ሁሉም በዘርፋቸው አጀንዳዎቻቸውን በማሰባሰብ ሁለንተናዊ ነገሮችን ለመያዝ ያስችላል፡፡

እንደ አንድ ሀገር ዜጎች የተቀራረበ አስተሳሰብ ልንይዝባቸው በሚገቡ ሃሳቦችና ጉዳዮች መሸርሸር ተከትሎ ሳይፈቱ የተንከባለሉ ወይም አዲስ የተፈጠሩ ችግሮች አሉ፡፡ ይህም ሀገሪቱ በየአካባቢው ግጭቶች እና መፈናቀል ያስከተለ ሲሆን፤ ያለው አሳሳቢ ሁኔታ ወደ ምክክር እንድትገባ የሚያስገድድ ነው ይላሉ፡፡

በምክክሩ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያስማማ ሃሳብ እንዲኖረን የማድረግ ዓላማ ያለው ነው፡፡ በዚህም ያለውን አለመግባባት ከማስቆም ባለፈም ወደበጎ መስመር በመቀየር በየዘርፉ የተሻለ አዲስ የዲሞክራሲያዊ ባህል መፍጠር ያስችላል ሲሉ ፕሮፌሰር አድማሱ ያመላክታሉ።

በመሆኑም ከየማህበረሰብ ክፍሎች የተመረጡ ተወካዮችና ባለድርሻ አካላት በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ ያለውን ፋይዳ በመረዳት ቁልፍ የሆኑ አጀንዳዎችን በማሰባሰብ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ኮሚሽነሩና አማካሪው እንደተናገሩት፤ የምክክር ሂደቱ ወሳኝ ምዕራፍ የሆነው የአጀንዳ ማሰባሰብ አሳታፊ፣ ግልጽና መፍትሔ የሚያመጣ ሂደቱን እንደተጠበቀ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።



# የውሃ ጥም ቆራጩ -...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ፕሮጀክት፡፡

ቦረናን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ፕሮጀክቱን እያስፋፋ የመጣው የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት፣ ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገነባቸው ግድቦች ለብዙዎች አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡ በጉምቢ ቦርደዴም የተገነባው የውሃ ግድብ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለውን ሆኗል፡፡ የውሃ ማቆሪያው በስፍራው መገንባቱ በአካባቢው ላሉት ነዋሪዎች እፎይታን ያጎናጸፈ ነው፡፡

የወረዳው ነዋሪ ከሆኑት መካከል ወጣት አርሶ እና አርብቶ አደር ሃመያስ ሁሴን፣ የግድቡ መገንባት በብዙ መልኩ እየጠቀማቸው መሆኑን ይናገራል፡፡ ቀደም ሲል ከብቶቻቸውን ውሃ ለማጠጣት ራቅ ወዳለ ስፍራ ማጓጓዝ ግድ ይለው እንደነበር የተናገረው ወጣቱ፤ አርሶ እና አርብቶ አደር፣ በአሁኑ ወቅት ግድቡ በአካባቢያቸው በመገኘቱ ትልቅ እፎይታን የሰጠ ነው ብሏል፡፡ ከብቶቻቸውን ይዘው ወደሩቅ ቦታ ውሃ ለማጠጣት በሚወስዱ ጊዜ የጊዜም የጉልበትም ብክነት መኖሩን አልሸሸገም፡፡ አሁን ከዚያ ሁሉ ውጣ ውረድ አረፍ ማለታቸውን ጠቅሶ፤ በዚህ ግድብ በቀጣይ የመስኖ ሥራም በሰፊው እንደሚሠራበት አስረድቷል፡፡

አርሶ እና አርብቶ አደር ሳኒዮ አደም ቦሮ በበኩላቸው፤ በግድቡ መገንባት ግንባር ቀደም ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ የእነርሱንም የከብቶቻቸውንም የውሃ ጥም የቆረጠ ፕሮጀክት መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ መንግሥት የሠራው ሥራ የሚመሰገን ነው፤ ከተገነባልንን ውሃ በመስኖ በማምረት ውጤታማ እንሆን ዘንድ የውሃ መሳቢያ ሞተር ቢገዛልን መልካም ነው ይላሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት እየተገደበ ያለ የውሃ ግድብ ገና ጅምር ነው የሚሉት ደግሞ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በጉምቢ ጎርደዴ፣ በሚኤሶ እና በሌሎች ወረዳዎች ተዘዋውረው የተለያዩ የልማት ሥራዎችን የጎበኙ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ናቸው፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ሕዝቡ ላለመለመን ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ዞኑ አንዳች ያጣው ነገር የለም፡፡ የተጀመረው የውሃ ጉዳይ ቀጣይነት የሚኖረው ነው፡፡ በተገኘው እድል ሁሉ መጠቀም ግን የሕዝቡ ምርጫ ነው፡፡

በተፈጠረው እድል በመጠቀም ከብቱንም ግመሉንም ማድለብ ከተቻለ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይችላል የሚሉት አቶ ሽመልስ፤ በተገደበው ውሃ በመታገዝ ልማቱንም ጎን ለጎን ማስኬድ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ በቀጣይም ወደ አካባቢው ሲመጡ በተሻለ ለምቶ እንደሚያዩም እምነታቸው መሆኑን ይናገራሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ከልማቱ ጎን ለጎን ሕዝቡ የራሱን ሰላም ለማስጠበቅ ቁርጠኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ወረዳዋ ቦርደዴ ጠላት የሚደበቅባት ሳትሆን ልማት የሚከናወንባት መሆን ይጠበቅባታል፡፡ ወረዳዋን የሚያተኩሳት ቆላማነትም ከልማቱ የተነሳ መቆም አለበት፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለቁጠባ ትልቁን ስፍራ መስጠትም መዘንጋት የለበትም፡፡

በልማቱም፣ በሰላሙም በኩል የጀመርናቸውን ሥራዎች አጠናክረን እንቀጥላለን ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዞኑ ሰፊ ሀብት ያለው እንደመሆኑ ለዚህ ሥራ ምቹ ነው ይላሉ፡፡ የአካባቢው በረሃማነትም ተቀይሮ ምቹ የሆኑ እንደ ሪዞርት አይነት መዝናኛ ስፍራዎች እንደሚሠሩም ያላቸውን እምነት ይገልጻሉ፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የሆርቲካልቸር ምርቶችን ልማት ማስፋፋትና ድንበር ማሻገር የሚያስችለው ስምምነት

**ማሕሌት አብዱል**

ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ምርቶች ተስማሚና ምቹ ሥነ-ምህዳር፣ የአየር ንብረትና ሰፊ የሰው ኃይል እንዳላት ይታወቃል። የሆርቲካልቸር ልማት በሀገሪቱ ከተጀመረ ሁለት አስርተ ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን፣ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ከሚያስገኙ የግብርና ምርቶች አንዱ ሆኗል።

ይሁን እንጂ የመንግሥትን ድጋፍ ጨምሮ በሀገሪቱ ለዘርፉ ምቹ ሁኔታ ያህል ዘርፉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ አስተማማኝና ሁነኛ የጀርባ አጥንት እንዲሆን ለማድረግ የተሠራው ሥራ እምብዛም መሆኑን የዘርፉ ተዋናዮች ይናገራሉ። ካለው እምቅ አቅም አንፃር ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ላይ ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች መኖራቸውንም ያነሳሉ። በተለይም በስፋትና በጥራት በማምረት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ላይ ክፍተቱ ጎልቶ እንደሚታይ ይጠቀሳሉ።

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር መረጃ እንደሚያሳየውም፤ በኢትዮጵያ በአበባ፣ በፍራፍሬ፣ በአትክልትና በመዓዛማ እፅዋት ልማት ዘርፍ 128 የሚደርሱ ኢንቨስትመንቶች ያሉ ሲሆን፣ 10 ሚሊዮን 897 ሺ ሄክታር መሬት በዘርፉ እየለማ ይገኛል። በዚህም 200 ሺ ለሚደርሱ ዜጎችም በዘርፉ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከዘርፉ 658 ነጥብ 30 ሚሊዮን ዶላር ማስገባት ተችሏል። በአሁኑ ወቅት ዘርፉ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ገቢ በማስገባት በአራተኛ ደረጃ ያለ ቢሆንም፣ ያለውን እምቅ አቅም በመጠቀም በስፋትና በጥራት ማምረት ቢቻል አሁን እየተገኘ ካለው ገቢ በላይ ማግኘት እንደሚቻል የመንግሥትም የዘርፉ ባለሙያዎችም እምነት ነው።

የግብርና ሚኒስቴር ሰሞኑን የኢትዮጵያን ሦስት የሆርቲካልቸር ምርቶች በስፋትና በጥራት በማምረት በተለያዩ የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገራት ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል ስምምነት ከሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማኅበርና ከኮሜሳ/የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ/አባል ሀገራት ጋር ከሰሞኑ መፈራረሙ ይታወሳል። ስምምነቱ ኢትዮጵያ የምታመርታቸውን በተለይም የሸንኩርት፣ አቦካዶና ድንች ምርቶችን በኮሜሳ አባል ሀገራት ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር የግብርና ምርቶችን ንግድ ለማሳለጥ እንደሚረዳ በስምምነቱ ወቅት ተገልጿል።

የግብርና ሚኒስቴርን በመወከል ስምምነቱን የፈረሙት የግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ ፕሮፌሰር ዓሊ መሐመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ኮሜሳ በምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገራት በንግድ የሚተባበሩበት ማኅበር እንደመሆኑ፣ የስምምነቱ መፈፀም ኢትዮጵያ የምታመርታቸው የሆርቲካልቸር ምርቶች የገበያ መዳረሻ እንዲሰፋ ያደርጋል።

የአባል ሀገራቱ የርስ በርስ የንግድ ልውውጥ ይበልጥ እንዲጠናከር በማድረግ በኩልም ስምምነቱ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም ሀገራቱ ምርታቸውን በጋራ በማቀናጀት ወደ ተለያዩ የዓለም ገበያዎች ለመላክና የላቀ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታንም ይፈጥራል። ከዚህም ባሻገር የግል ባለሃብቶች የግብርና ሥራቸውን ማስፋፋት የሚያስችላቸውን የፋይናንስ፣ የግብዓት፣ የቴክኖሎጂ ድጋፎችን እንዲያገኙ የሚያደርግ ሲሆን፤ በተለይም አነስተኛ አምራቾች አቅማቸው እንዲጎለብት የላቀ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

«በዋናነትም አምራቾቹ ከመንገድ፤ ከማቀዝቀዣና ከመሰል ግብዓቶች ጋር በተያየዘ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትም አቅም ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል» ያሉት ፕሮፌሰር ዓሊ፤ በስምምነቱ መሠረት ይህ በጋራ የሚሠራበት የጋራ ፕሮጀክት ከሦስት እስከ አምስት ዓመት እንደሚቆይም አስታውቀዋል። ስምምነቱ እንደየሁኔታውና እንደየአስፈላጊነቱ እየታየም በየጊዜው የሚታደስ ይሆናል ብለዋል። የአባል ሀገራቱን በጋራ ተቀናጅቶ የመሥራት ዕድልንም እንደሚያሰፋው ተናግረው፤ በተለይም የግል ባለሃብቶች ፋይናንስ እንዲያገኙና የሆርቲካልቸር ልማቱን ለማስፋፋት እንደሚያግዛቸው ያስረዳሉ።

እንደ ፕሮፌሰር ዓሊ ገለፃ፤ የሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ለሀገር ኢኮኖሚ ጠቀሜታው ሰፊ ቢሆንም እስካሁን ባለው እምቅ አቅም ልክ ያለመሠራቱ ያስቆጫል። ከኮሜሳ ጋር የተመሠረተው የጋራ ትብብር ትልቁ ጠቀሜታም ምርትን ከአንድ ሃገር ወደ ሌላ ሃገር ከመውሰድ በዘለለ ጥራት ያለው ምርት በስፋት ለማምረት የሚያግዝ ነው። ይህም የሚሆነው የኢትዮጵያ ምርቶች በሁሉም የገበያ መዳረሻዎች ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ የጥራት ደረጃውና የምግብ ደኅንነታቸውን መረጋገጥ ሲቻል ነው።

«ከሌሎቹ ሃገራት ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘትና በገበያው ላይ በተሻለ መልኩ ተፈላጊ ለመሆን አግባብነት ያለው የእርሻ አሠራር መከተል አለብን» የሚሉት አማካሪው፤ በተለይም አምራቹ ኃይል ከሚጠቀመው ማዳበሪያ ጀምሮ በዘር፣ በምርት መሰብሰብና ታሽጎ ወደሚፈለግበት ስፍራ እስከሚደርስ ድረስ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሠራት የሚጠበቅበት መሆኑን ያስረዳሉ።

መንግሥትም ሆነ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የምርቱን ጥራት የማረጋገጥ ሥራ መሥራት እንዳለባቸውም ያስገነዝባሉ። ይህንን ማድረግ ከተቻለ የኢትዮጵያ ምርቶች አይደለም የአፍሪካ ገበያን የዓለምን ገበያም መቆጣጠር የማይችሉበት ሁኔታ እንደማይኖር አመላክተዋል።

በተለይም የግሉ ዘርፍ ትልቁን ሚና መጫወት እንደሚጠበቅበት የተናገሩት ፕሮፌሰር ዓሊ፤ መንግሥትም የግሉን ዘርፍ አቅም ለማጠናከር የተለያዩ የድጋፍና ክትትል ሥርዓቶችን በመዘርጋት እየሠራ መሆኑን ይጠቁማሉ። ከእነዚህም መካከል ሁሉንም የዘርፉን ተዋናዮች ተሳታፊ የሚያደርግ ጉባኤ መኖሩን ጠቅሰው፤ በዚህም በቅርበት በመሆን ችግሮች ላይ በመምከርና የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚሠራበት አግባብ መኖሩንም ያስረዳሉ።

«የዚህ ስምምነት መፈፀም የሀገር ውስጥ የግል ዘርፉ ተዋናዮች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል» ያሉት አማካሪው፤ ይህም ከጎረቤት ሃገራት ጋር በሚኖረው የግብርና ምርቶች የንግድ ልውውጥ ከማሳለጥ ባለፈ የኢኮኖሚ ትብብራቸው እንዲጠናከርም አወንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ያመለክታሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ስምምነቱ የአፍሪካ ነፃ ገበያን ከማሳለጥ አኳያም አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። ከዚህ ባሻገርም ከዘር አቅርቦት ጀምሮ ባሉ የእሴት ሠንሠለቶች ሁሉ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ሲታይም የስምምነቱ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።

«ሆርቲካልቸር በተፈጥሮው በአንድ ሄክታር እስከ 30 ሰው ይፈልጋል፤ በተለይ ለወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራል» ሲሉም አስታውቀዋል። በአሁኑ ወቅትም የዘር ብዜት ሥራ መጀመሩን ጠቅሰው፤ በዚህም በርካታ ሰዎች እየተሳተፉ መሆናቸውን ይናገራሉ።

እንደአማካሪው ማብራሪያ፤ በስምምነቱ መሠረት በስፋት ለማምረትና ለመላክ የተመረጡት ሦስት የሰብል ዓይነቶች ናቸው፤ ይህም የተደረገው የምግብ ዋስትንና ሥርዓተ ምግብን ከማጠናከር አኳያ ያላቸው ፋይዳ ታይቶ ነው። ሰብሎቹ በአፍሪካም ሆነ በሌሎች የዓለም ሀገራት ተፈላጊና ለምግብነት የሚውሉ በመሆናቸው አሁን ከተጀመረውም በላይ በስፋት በማምረት ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለማስገባት ይሠራል።

በአሁኑ ወቅት በተለይ በአቦካዶ ላይ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚደረግ ሲሆን፣ ሽንኩርትም በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ ከተካተቱ ወሳኝ ሰብሎች አንዱ እንደመሆኑ በጥራትና በስፋት እንዲመረት የሚደረግ ይሆናል። በተጨማሪም ድንች በተለይ ለአግሮ ኢንዱስትሪው ሁነኛ ግብዓት በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲመረት ይደረጋል።

በግብርና ሚኒስቴር የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ አብደላ ነጋሽ በበኩላቸው በሀገሪቱ በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ «በተለይም አሁን ላይ ባለው የዓለም ነባራዊ ሁኔታ በሀገር ውስጥ ብቻ ተወስኖ መሥራቱ ውጤት እንደማያመጣ ታምኖበት የምርቶቹን መዳረሻ ሀገራት ለማስፋት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው» ይላሉ። በመሆኑም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ሀገራት ብሎም ራቅ ላሉት የዓለም ኅብረተሰቦች




**ስምምነቱ በተፈረመበት ወቅት**

በማምረት ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፉ መጠቀም ያለባትን ሁሉ እንድታገኝ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ያብራራሉ።

«ከዚህ አንፃር ወደ ዓለም አቀፍ ትብብሮች ከመግባታችን በፊት በቀጣና ደረጃ በተለይ ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ያስፈልጋል የሚል እምነት ይዘን ነው ከኮሜሳ አባላት ሀገራት ጋር በጋራ ለመሥራት የተስማማነው» የሚሉት አቶ አብደላ፤ ከዚህ አንፃር ቢልኤንድ ሜሊንዳ ጌት ፋውንዴሽን የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ስለመሆኑ ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም በእሴት ሠንሠለት ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

በዚህም ከአምራቹ እስከ ኢንዱስትሪ ድረስ በአጠቃላይ በእሴት ሠንሠለቱ ያሉ ተዋናዮች የሚያሳተፉበት መሆኑን መሪ ሥራ አስፈፃሚው ተናግረው፤ «ይህም ለሆርቲካልቸር ልማቱ ውጤታማነት ሰፊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለን ነው የምናስበው» ይላሉ። በሆርቲካልቸር ምርቶች ላይ ጥራትን መሠረት ያደረገ የአመራረት ዘዴ በመከተል፤ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ሀገርም በሚፈልገው የጥራት ደረጃ ማምረት እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ።

በተለይም አብዛኞቹ የሆርቲካልቸር ምርቶች ቶሎ የሚበላሹ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በስፋት ከማምረት በዘለለ በጥራትና በጥንቃቄ ጠብቆ ማድረስ እንደሚጠይቅ ተናግረዋል። ለእዚህም በእሴት ሠንሠለቱ ያሉ አካላት ያልተቋረጠ ጥረት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ይህ ሲሆንም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንደምታገኝ አስታውቀዋል።

የኮሜሳ ተወካይና የአሊያንስ ፎር ኮሞዲቲ ትሬድ ኢን ኢስት ኤንድ ሳውዝ አፍሪካ (አክትሳ) ሥራ አስፈፃሚ ጆን ሙካካ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ስምምነቱ የሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪው በተለይም በአባል ሀገራቱ እየተንቀሳቀሰ ያለውን ሃብት በሦስት እጥፍ ለማሳደግ የሚያስችል ነው። ይህም በዋናነት የግሉ ዘርፍ ተዋናዮችና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አነስተኛ ገበሬዎች በምርታቸው የላቀ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያግዛል። በሀገራቱ መካከል በሚፈጠረው የገበያ ትስስር አማካኝነት የንግድ ልውውጥ ብቻ ሳይሆን ተሞክሮ በመቀመር ምርታማነታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ አቅም የሚሰጣቸው ይሆናል።

ስምምነቱ በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ያሉ አምስት ሀገራት የሆርቲካልቸር ምርቶች ንግድ ልውውጥ ይበልጥ እንዲጠናከር፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲመዘገብ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት ዶክተር ጆን ያስገነዝባሉ። በዋናነትም መካከለኛ፣ አነስተኛ አምራቾች የፋይናንስ አቅርቦት እንዲመቻችላቸው፤ የአመራረት ሂደታቸውን እንዲያዘምኑ፣ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር እንዲሁም ሥልጠና እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግም የስምምነቱ አካል መሆኑን ያመለክታሉ።

የሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ምቹ ከሆኑ ጥቂት የዓለም ሀገራት መካከል ትመደባለች። ከዚህ አንፃር ባለፉት ዓመታት ዘርፉ መጠነኛ የሚባል እድገት ከማስመዝገብ ባለፈ በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ በሥራ ፈጠራና በሌሎችም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አነስተኛ አስተዋፅዖ እያደረገ ነው። ይህ የሆነውም በዋናነት በመሬት፣ በፋይናንስና የሎጀስቲክስ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ባሉ ችግሮች ምክንያት ነው። በተለይም ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሃገራት ጭምር ማቅረብ የሚያስችል አቅም ቢኖራትም፣ ይህንን አቅም መጠቀም ላይ ውስንነት ይስተዋላል ።

ስምምነቱ በተለይም በኮሜሳ ውስጥ ያሉ 21 ሀገራትን ያቀፈ እንደመሆኑ በተለይም እንደ ኬንያ ያሉና በዘርፉ የተሻለ ምርጥ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ልምድ በመቀመር ወደ ሀገር ውስጥ ማምጣት ያስችላል። በቀጣናው ላይ ፖሊሲዎች ወደአንድ መጥተው እውቀትና ተሞክሮ የሚዳቀልበትና የተሻለ አፈፃፀም የሚመዘገብበት ሁኔታ እንዲፈጠር ይረዳል ተብሎ ይታመናል።

አቶ ፋሲካ ሥዩም ፍሪ-ኤል ኢትዮጵያ የተሰኘ የሆርቲካልቸር አምራች ኩባንያ ቢዝነስ ኦፕሬሽን ማናጀር ናቸው። እርሳቸው እንደገለፁት፤ ስምምነቱ የኢትዮጵያን የሆርቲካልቸር ዘርፍ ወደፊት የሚያራምድ ከመሆኑም ባሻገር አምራቹ በስፋት እንዲያመርትና ለሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኝ ያደርጋል። በዚህ ረገድ መንግሥት ከኮሜሳ ጋር ካደረገው ስምምነት በተጨማሪ ባለፉት ዓመታት ዘርፉን ለማሳደግና የሚገኘውን ገቢ ከፍ ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው።

በሀገሪቱ በሆርቲካልቸር ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት በኩል መሻሻሎች እየታዩ መምጣታቸውን አቶ ፋሲካ ይናገራሉ። «በተለይም ከግብዓትና ሎጀስቲክስ አቅርቦት አኳያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ረገድ መሻሻሎች እየታዩ ናቸው። ከሠላምና ደኅንነት ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች አሁንም የአምራች ኃይሉ ስጋት ናቸው» ይላሉ። በተለይም የእርሳቸው ድርጅት እርሻ ደቡብ ኦሞ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ ብዙ ክልሎችንና ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ መጓዝን እንደሚጠይቅና የሠላም ጉዳይ አንገብጋቢ ጉዳዩ መሆኑን ጠቅሰዋል።

«በግጭት ምክንያት መንገዶች ሲዘጉ ብዙ ምርት የሚበላሹበት ሁኔታ ያጋጥመናል፤ ይህ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ካልተሰጠውና አስተማማኝ ሠላም ማስፈን ካልተቻለ የሀገሪቱን ምርት ለውጭ ገበያው በስፋት ተደራሽ ለማድረግ ለተያዘው ሀገራዊ ጥረት እንቅፋት እንዳይሆን ስጋት አለኝ» ይላሉ። በየመንገዱ ባሉ ኬላዎች ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች አሁን እየተቃለሉ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። እንደተሸከርካሪ ያሉ ቁሳቁስን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ላይ በአንዳንድ ተቋማት የሚጋጥመው ቢሮክራሲ የበዛበት አሠራር መሻሻል እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የአዲሱ ትምህርት ዘመን የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች

አስናቀ ፀጋዬ

የ2017 ዓም የትምህርት ዘመን ሊጀመር ከአንድ ወር ያነሰ ጊዜ ብቻ ይቀረዋል። በዚህ ወር እንደተለመደው የትምህርት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ። ከነዚህ ውስጥ ተማሪዎችን መመዝገብ፣ የትምህርት ቤቶችን ምድረ ግቢ ማፅዳትና አመቺ የማድረግ፣ የመማሪያ ክፍሎችን ማደስና ለመማር ማስተማር ሂደት ወሳኝ የሆኑ ግብዓቶችን የማሟላት ሥራዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። ይህ ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የማድረግ ሥራ ከዚህ ቀደምም የነበረና አሁንም እየተሠራ ያለ ነው። ይሁንና ይህ ሥራ በፊት ከነበረው ልዩ የሚያደርገው የትምህርት ቤት ማደስ ሥራው ባለሀብቶችንና የትምህርት ቤት ማኅበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ መከናወኑ ነው።

በተለይ ባለሀብቶች በትምህርት ቤቶች ማደስ ሥራ መሳተፋቸው ትምህርት ቤቶች ከዚህ በፊት ከነበራቸው ይዞታ የተሻለ ገፅታ እንዲላበሱና ለመማር ማስተማር ሂደት ይበልጥ አመቺ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ለዚህ ሥራ ደግሞ በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለሀብቶችንና የትምህርት ቤት ማኅበረሰቡን በማስተባበር ትልቁን ድርሻ ወስዷል። የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮም የትምህርት አመራሮችን፣ መምህራንን፣ የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራንን፣ ወላጆችንና ተማሪዎችን በማሳመንና በማስተባበር የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል።

በትምህርት ቅድመ ዝግጅት ሥራ ትምህርት ቤቶችን ከማደስና ለመማር ማስተማር ሂደቱ አመቺ ከማድረግ በዘለለ ለአካል ጉዳተኞችና ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አስፈላጊ ግብዓቶችን የማሟላትና ለእነርሱ አመቺ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራዎችም በስፋት ተከናውነዋል። ለልዩ ፍላጎትና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ አመቺ የመማር ማስተማር ምሕዳር በመፈጠሩ በትምህርት ውጤታቸው ላይ ለውጥ መምጣት ችሏል። ይህንንም የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የ2016 ዓ.ም አፈፃፀምን ለከተማው ምክር ቤት ሪፖርት ባደረገበት ወቅት አስታውቋል።


በሌላ አባባል ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማር አመቺ ማድረግ ለአካል ጉዳተኞችና ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለመደበኛ ተማሪዎች ውጤት መሻሻልም አይነተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ያመለክታል። ትምህርት ቤቶችን ውብ፣ ማራኪና ለመማር ማስተማር አመቺ የማድረጉ ሥራ በተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ ከሚኖረው በጎ ተፅዕኖ ባለፈ በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ፈርጀ ብዙ ልዩነት በማጥበብ ረገድም ሚናው የጎላ ነው። በተጨማሪም በትምህርት ቤቶቹ መካከል የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የሚደረገውን የፉክክር መንፈስ ያሳድጋል።

ከዚህ ባሻገር ከዚህ በፊት የነበረውን የትምህርት ቤቶች ደረጃ በማሳደግ ለዘመኑ የሚመጥኑ ትምህርት ቤቶችን ለመፍጠርና የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ ትልቅ ሚና አለው። ይህ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቶችን በዚህ ደረጃ መሥራት ከዚህ ቀደም በማኅበረሰቡ በኩል የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የወረዱና በተገቢው ልክ ትምህርት የማይሰጥባቸው እንደሆኑ የሚቆጠሩበትን የተሳሳተ አመለካከት በመቀየር ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው።

ወላጆችም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ያላቸው አመኔታ እንዲጨምርና ልጆቻቸውን ወደትምህርት ገበታ እንዲልኩ ይበልጥ መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል። ትምህርት ቤቶቹ በአከባቢው ማኅበረሰብና ባለሀብቶች ደረጃቸውን ጠብቀው መገንባታቸውና መታደሳቸው ደግሞ ወላጆች የባለቤትነት ስሜት እንዲላበሱ ያደርጋል።

እንዲያም ሆኖ ትምህርት ቤቶችን አዲስ ገፅታ የማላበስና ለመማር ማስተማር አመቺ የማድረግ ሥራ ወረትና የአንድ ወቅት ሥራ ብቻ እንዳይሆን የብዙዎች ስጋት ነው። ስለዚህ ሥራው የወረትና የአንድ ሰሞን ብቻ እንዳይሆን ከከተማ አስተዳደሩ፣ ከከተማው ትምህርት ቢሮ፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከወላጆች ብዙ ይጠበቃል ።

የከተማ አስተዳደሩ የጀመረው ሥራ በተማሪዎች ውጤትና ትምህርት ጥራት ላይ ተግባራዊ ለውጥ ማምጣቱን በመገንዘብ ትምህርት ቤቶችን የማደስና ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ የማድረግ ሥራ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። በተለይ ባለሀብቶችና የትምህርት ማኅበረሰቡ የጀመሩትን ትምህርት ቤቶችን የማደስና አመቺ የማድረግ ሥራ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ከእነርሱ ጋር በቅንጅትና በተግባቦት ብሎም ሁለንተናዊ ድጋፍ በመድረግ ሊሠራ ይገባል።



ትምህርት ቤቶችን ከማደስና ለመማር ማስተማር ምቹ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች ተከናውነዋል፣

የከተማው ትምህርት ቢሮ አመራሮችም ቢሆኑ ይህ ሥራ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ እንዲቀጥል ታች ድረስ ወርደው የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶችንና ትምህርት ቤቶችን መደገፍና ክትትል ማድረግ እንዲሁም ለዚህ ሥራ በንቃት እንዲሳተፉ መቀስቀስ ይጠበቅባቸዋል። በዋናነት ከነባሮቹ በተጨማሪ ሌሎች ባለሀብቶችን በማፈላለግ በትምህርት ቤቶች እድሳትና አመቺ የማድረግ ሥራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ማኅበረሰቡም በዚሁ ሥራ ልክ እንደባለሀብቱ ሁሉ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን አመራሮቹ ግፊት ማድረግ አለባቸው።

ትምህርት ቤቶች በተለይ መምህራንና ርዕሰ መምህራን በዚህ ሥራ ዋና ተዋንያን እንደመሆናቸው ደረጃቸውን ጠብቀው የተገነቡ፣ መልሰው የታደሱና ለመማር ማስተማር ሁኔታ አመቺ ተደርገው የተሠሩ ትምህርት ቤቶችን እንዳይጎዱ የመጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ለዚህ ደግሞ በተለይ ተማሪዎችን የማሳመንና ትምህርት ቤቶቹን እንደራሳቸው ንብረት እንዲጠብቁ የማስተማር ግዴታ አለባቸው።

ትምህርት ቤቶች መጪው ትውልድም ጭምር የሚማርባቸው እንደመሆናቸው ደረጃቸውን ጠብቀው ረጅም ግዜ አገልግሎት እንዲሰጡ ተማሪዎች በባለቤትነት ስሜት የትምህርት ቤቶችን ንብረት መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ወላጆችም ይህን አውቀው ልጆቻቸውን ትምህርት ቤቶቻቸውን እንዲጠብቁና ትምህርት ቤቶችን ንብረት በአግባቡ እንዲጠቀሙ መገሰፅና መምከር አለባቸው። ስለዚህ ከከተማ አስተዳደሩ ጀምሮ ሁሉም የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ የሚጠበቅበትን ድርሻ ሲወጣ ተማሪዎች በደረጃቸውን በጠበቁና በተሻሉ ትምህርት ቤት ተምረው ውጤታቸውን ማሻሻል ይችላሉ። የትምህርት ጥራትም ይረጋገጣል።

ትምህርት ቤቶችን ከማደስና ለመማር ማስተማር ምቹ ከማደረግ ባለፈ በትምህርት ቅድመ ዝግጅት ሥራው ከወዲሁ እየተከናወኑ ካሉ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ትምህርት ቤቶች በቴክኖሎጂ እንዲዘምኑ የማድረግ ሥራ ነው። በዚሁ መነሻነት የ2017 ዓ.ም የተማሪዎች ምዝገባ በሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ኦንላይን እንደሚካሄድ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ከሳምንታት በፊት አስታውቋል። ትምህርት ቤቶችም ይህን አውቀው ከወዲሁ በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባቸው ቢሮው ገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማትና ማስፋት ዳይሬክቶሬት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን የተማሪዎችን ምዝገባ ኦን ላይን

**ትምህርት ቤቶችን ውብ፣ ማራኪና ለመማር ማስተማር አመቺ የማድረጉ ሥራ በተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ ከሚኖረው በጎ ተፅዕኖ ባለፈ በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ፈርጀ ብዙ ልዩነት በማጥበብ ረገድም ሚናው የጎላ ነው**

ለማካሄድ በለማው የኢ ስኩል ቴክኖሎጂ ዙሪያ ለርዕሳነ መምህራን ጨምሮ ለአይ ሲቲ እና መረጃ ባለሙያዎች በዙር ሥልጠና ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ወንድሙ ኡመር በሥልጠናው ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ቢሮው ላለፉት ሁለት ዓመታት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን የ «ኢ ስኩል» ፕሮጀክትን በመቅረጽ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ገልፀዋል። በዚህ ቴክኖሎጂ አማካይነት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ የተማሪዎች ምዝገባን በሲስተሙ አማካይነት ኦን ላይን ማካሄድ እንደመሆኑ ሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ኦንላይን በመመዝገብ ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

ትምህርት ቤቶች ለምዝገባው የሚያስፈልጉ ኮምፒውተሮችን ጨምሮ የኢንተርኔት መሠረተ ልማቶችን ከወዲሁ ዝግጁ በማድረግ የምዝገባው ሂደት ስኬታማ እንዲሆን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንደሚገባቸውም ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገልጸዋል።

የ «ኢ ስኩል» ፕሮጀክት የመማር ማስተማር ሂደቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ከማድረጉ ባሻገር ፖሊሲ አውጪዎችም ሆኑ በጀት መዳቢ አካላት ከትምህርት ጋር የተገናኙ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የሚያስችል ሲስተም መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ዮናስ ተገኝ ጠቁመዋል። ምዝገባው በትምህርት ቤት መረጃ አስተዳደር ሲስተም (school information management system) አማካይነት የሚካሄድ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በመጀመሪያው ዙር ቂርቆስ ልደታ እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ርዕሳነ መምህራን እንዲሁም የአይ ሲቲ እና መረጃ ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን በቀጣይ ለቀሪ ክፍለ ከተሞችም ተመሳሳይ ሥልጠና እንደሚሰጥ ታውቋል። ይህም ለትምህርት ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በበቂ ሁኔታ ከሟሟላት ባሻገር በቴክኖሎጂ እንዲዘምኑ በከተማ አስተዳደሩ በኩል የሚደረገውን ጥረት ያሳያል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከትምህርት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ2017 የትምህርት ዘመን የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ ይፋ ተደርጓል። በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ የመንግሥት፣ የግልና በሌሎች የተያዙ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ወጥነት ያለው የትምህርት አተገባበር በማስፈለጉ የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ /የትምህርት ካላንደር/ እንደተዘጋጀም ነው የተጠቆመው።

በዚሁ መሠረት ከሰኔ 24 እስከ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የነባር ተማሪዎች ምዝገባ እና የመጽሐፍት ስርጭት እንደሚካሄድ፣ ከነሐሴ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ መምህራን በትምህርት ቤታቸው ተገኝተው ሪፖርት በማድረግ አጠቃላይ የመምህራን ጉባኤ እንደሚደረግ፣ ከነሐሴ 21-30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የ7ተኛ እና የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ምዝገባ እንደሚከናወን ተገልጿል።

ከጳጉሜ 1 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን ድረስ አስፈላጊውን መረጃ አሟልተው የሚመጡ አዲስ የተማሪዎች ምዝገባ እንደሚካሄድ ፣መስከረም 3 ቀን 2017 ዓ.ም ለተማሪዎች ስለ ትምህርት ቤቶች ሕገ ደንብና ተያያዥ ጉዳይ ላይ ገለጻ እንደሚሰጥ፣ መስከረም 6 ቀን 2017 ዓ.ም መደበኛ ትምህርት እንደሚጀመር፣ መስከረም 13 ቀን 2017 ዓ.ም ትምህርት በሬዲዮ ስርጭት እንደሚጀምር ተጠቁሟል።

ከኅዳር 16-18 ቀን 2017 ዓ.ም አንደኛ ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና እንደሚሰጥ፣ ከጥር 7-9 ቀን 2017 ዓ.ም ለ6ኛ፣ ለ8ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና እንደሚሰጥ፣ ከጥር 19-23 ቀን 2017 ዓ.ም አንደኛ ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና እንደሚካሄድ፣ ከጥር 26-29 ቀን 2017 ዓ.ም መምህራን ፈተና የሚያርሙበት እና ውጤት ማጠናቀሪያ ሳምንት እንደሆነ፣ ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም መምህራን የተማሪዎችን የፈተና ውጤት የሚያሳውቁበት መሆኑ ተነግሯል።

የካቲት 3 ቀን 2017 ዓ.ም የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት እንደሚጀመር፣ ሚያዚያ 6-8 ቀን 2017 ዓ.ም የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት አጋማሽ ፈተና እንደሚሰጥ፣ ግንቦት 19-22 ቀን 2017 ለ6ኛ፣ ለ8ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና እንደሚሰጥ፣ ከሰኔ 3-4 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የ8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ መልቀቂያ ፈተና እንደሚካሄድ፣ ከሰኔ 9-11 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የ6ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና እንደሚሰጥ፣ ከሰኔ 16-20 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና እንደሚከናወን፣ ሰኔ 26 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ መምህራን የተማሪዎችን የፈተና ውጤት የሚያሳውቁበት እንደሚሆንና ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ.ም የውጤት መግለጫ ካርድ በመስጠት የዓመቱ ትምህርት እንደሚጠናቀቅ ታውቋል።

# ‹‹ቡና ሲነሳ በበቃ እርሻ ልማት ድርጅትም አብሮ ይነሳል››

**አቶ ሁነኛው ጥላዬ**

**በበበቃ ቡና እርሻ ልማት ድርጅት የእርሻ ክፍል ኃላፊ**

ስምስም መንግሥቱ

አረንጓዴው ወርቅ እየተባለ የሚሞካሸውና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥም የአንበሳውን ድርሻ የያዘው የቡና ጉዳይ ሲነሳ የበበቃ ቡና እርሻ ልማት ድርጅት አብሮ ይነሳል። በተለይም ከአራት አስርት ዓመታት በፊት የነበረው ትውልድ ስለዚህ የልማት ድርጅት በደንብ ያስታውሳል። ‹‹የኢኮኖሚ ዋልታ ቡና፣ ቡና...›› እየተባለ በሚዘመርበት ዘመን የልማት ድርጅቱም ስምና ዝና አብሮ ይነሳ ነበር።

በበቃ በኢትዮጵያ እድሜ ጠገብና ትልቁ የቡና ልማት ድርጅት ሲሆን፤ በሀገር ባለውለታነቱም ይጠቀሳል። የልማት ድርጅቱን ያቋቋመው የደርግ መንግሥት ድርጅቱን ሲያቋቁም እንደሀገር የቡና ምርታማነት እንዲጨምርና በሀገር ኢኮኖሚ ላይም አስተዋፅዖው ከፍ እንዲል ለማስቻል እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በበቃ መጀመሪያ ሲቋቋም መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ሆኖ ነው የተቋቋመው። ከሚዛን ተፈሪ በ28 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው። በበቃ በዓለም ገበያ ተፈላጊ የሆኑና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትም የላቀ ሚና ያላቸው የተለያዩ የቅመማቅመም ልማቶችን ለማከናወን በሚያስችል ምቹ አካባቢ ነው የሚገኘው።

በበቃ የመንግሥት እርሻ ልማት ሆኖ ለረጅም ጊዜ የሠራ ቢሆንም በመንግሥታዊ ይዞታነቱ አልቀጠለም። በአሁኑ ጊዜ ልማት ድርጅቱ በሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ሥር ሆኖ ነው ልማቱን እያከናወነ የሚገኘው።

በአሁኑ ወቅትም በሜድሮክ ስር ሆኖ 95 በመቶ ድርሻ በመውሰድ በጥራትም በብዛትም ቡና እያለማ ለዓለም ገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛል። በተጓዳኝም ቁንዶበርበሬና እርድ ቅመሞችን ያለማል። ኩባንያው ወደፊትም ከቡናው በተጨማሪ በከፍተኛ ሁኔታ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ልማቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ለመሥራት አቅዷል። አጠቃላይ የልማት ድርጅቱን እንቅስቃሴ በተመለከተ በበቃ ቡና እርሻ ልማት ድርጅት የእርሻ ክፍል ኃላፊ ከአቶ ሁነኛው ጥላዬ ጋር ቆይታ አድርገናል። ውድ አንባቢያንም መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

**አዲስ ዘመን፤ እስኪ በቅድሚያ ስለበበቃ እርሻ ልማት ምሥረታ መለስ ብለው ያስታውሱን?**

**አቶ ሁነኛው፤-** በበቃ እርሻ ልማት መንግሥታዊ ድርጅት ሆኖ የተመሠረተ ሲሆን፤ የተመሠረተውም በዋናነት ለቡና ለልማት እንዲውል ነው። ተቋሙ እንዲመሠረት ሀገሪቱ ያፈራቻቸው ትላልቅ ባለሙያዎች ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል። ብዙ ሰዎች ተሳትፎ አድርገው ሙያዊ አስተዋፅዋቸውን አበርክተዋል። አሁንም ዋና ልማቱ ቡና ነው። በተጓዳኝ ግን ቅመማቅመምና የበቆሎ እርሻ ሥራ ያከናውናል። የበቆሎ ምርት ለገበያ ሳይሆን በአብዛኛው ለሠራተኛ ነው የሚውለው።

በበቃ እርሻ ልማት በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው የተቋቋመው። በኩታገጠም በሰፊ የቡና ማሣ ላይ የቡና ልማት የሚካሄድበት አካባቢ ነው። ይህም በሀገራችን ብቻ ሳይሆን፤ በምሥራቅ አፍሪካም ተጠቃሽ ነው። በ10ሺ ሄክታር ክልል ውስጥ ነው የሚገኘው። ከዚህ ውስጥ ለአካባቢው የአየር ንብረት መጠበቂያ ተብለው የማይነኩ ከጫካና ረግረጋማ ቦታዎች በስተቀር ወደ ስድስት ሺህ ሄክታር የሚሆነው መሬት በተለያየ የሰብል ልማት የተሸፈነ ነው።

በበቃ ቡና እርሻ ከ2003 ዓ.ም. ነሐሴ ወር ጀምሮ ከመንግሥት ይዞታነት ወጥቶ ወደ ግል ተዛውሯል። አሁን ላይ እርሻ ልማቱን የሚያስተዳድረው ሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ነው። ኩባንያው ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ልማቱን አጠናክሮ ቀጥሏል። ልማቱ ከኩባንያው ተጠቃሚነት አልፎ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አወንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት በአደረጃጀትና በምርታማነት በየጊዜው ለውጥ በማድረግ ላይ ይገኛል። እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችም ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ለውጥ እያስገኙ ነው።

አካባቢው ለቡና ተስማሚ የሚባል ነው። ሆኖም



ፎቶ ዳኜ አበራ

ግን የአየር ፀባዩ እንደሚባለው ከፍተኛ የሆነ የቡና መጠን የሚያስገኝ ነው ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር አያስደፍርም። በበቃ እርሻ ልማት ለዘመናት ሲያመርት የነበረው በሄክታር ከሁለት ኩንታል የበለጠ አልነበረም። ሜድሮክ ኩባንያ በዚህ በኩል የወሰደው እርምጃ እራሱም የጥናት ሥራው አካል ሆኖ ለአካባቢው የአየር ፀባይ ተስማሚ የሆነ አዲስ የቡና ዝርያዎች የሚለሙበትን መንገድ አመቻችቷል።

ከ86 በመቶ በላይ የቡና ዝርያዎች ተቀይረዋል። በአሁኑ ጊዜም በጅማ እርሻ ምርምር ማዕከል በጥናት የወጡ የተለያየ ዝርያ ያላቸው የቡና ችግኞች እየተለቀቁ ነው። ሀገራዊ ስም እየተሰጣቸው ከምርምር እንዲወጡ እየተደረገ ሲሆን፣ ስያሜ የመስጠቱ ሂደት ገና አልተጠናቀቀም። የምርምር ሥራው እና ሂደቱ የተካሄደው ልማቱ በሚገኝበት የኩባንያው ድርጅት ውስጥ ነው። በዚህ መልኩ ለአካባቢው የአየር ፀባይ የሚስማሙ የቡና ዝርያዎችን ማግኘት ተችሏል። ኩባንያው ወደፊት በስጦታና በተለያየ መንገድ የአካባቢው አርሶ አደርም እንዲጠቀም የማድረግ እቅድ አለው።

ኩባንያው የቡና ዝርያዎች መቀየር ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የነበረው። ለድርጅቱ ሥራ መለወጥና እድገት እንዲሁም እንደሀገር ጉልህ አስተዋፅዖ እንዲኖረው አስችሎታል። በአሁኑ ጊዜ የሚሰበሰበው ቡና በሄክታር ከሰባት እስከ አስር ኩንታል አንዳንዴም ከዚያ በላይ ይሆናል። ይህን ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው ዝርያ በመለወጥ ብቻ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። የተለያዩ ግብዓቶችንም በመጠቀም ጭምር ነው። የማዳበሪያ አቅርቦትና የአፈሩ ተስማሚነት ሁሉ በደንብ ይታያል። በተለይም አፈር ምርመራ ላይ በልዩ ጥንቃቄ ይሠራል። በየሁለት ዓመቱ የአፈር ምርመራ ይደረጋል። የጎደለው ንጥረነገር ካለም ሳይንሱን ተከትሎ ይሟላል።

በአጠቃላይ የቡና ምርታማነትን ለማሳደግ ከጥናት ሥራ እስከ ችግኝ ማፍላት ድረስ ባለው ሂደት በልዩ ትኩረት ነው የተሠራው። በሥራው ላይም ቁርጠኛ አመራሮች ባይኖሩና ያላሰለሰ ጥረት ባያደርጉ ኖሮ ለውጥ ማምጣት አይቻልም ነበር። ለውጡን ለማምጣትም ከፍተኛ የገንዘብ ወጪም ተደርጓል።

በአጠቃላይ ኩባንያው በእውቀት ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጭ በማድረግ ነው ለውጥ ያመጣው። በአንድ ዓመት ብቻ ከአንድ ሺ ሄክታር መሬት ላይ አሮጌ ቡና ተነቅሎ በአዲስ ተተክቷል። ቡና ምርት የሚሰጠው በሦስት ዓመት ነው። ይሁን እንጂ ወደፊት የሚገኘውን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ ነው እርምጃው የወሰደው። ይሄን ጊዜ ለመጠበቅ ሲወሰንም ቁርጠኝነትን ነው የሚሳየው።

ለውጡ አዲስ እይታ ነው ማለት ይቻላል። እንደሀገርም ከፍተኛ ቡና እንዲመረት የበኩላችንን ጥረት አድርገናል፤ ለውጥም አምጥተናል። አሁን ላይ

> **በበቃ በዓለም ገበያ ተፈላጊ የሆኑና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትም የላቀ ሚና ያላቸው የተለያዩ የቅመማቅመም ልማቶችን ለማከናወን በሚያስችል ምቹ አካባቢ ነው የሚገኘው**

አፍ ሞልተን ስለለውጡም መናገር የቻልነው መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሥራ በመሠራቱ ነው። ቁርጠኛ እርምጃ ተወስዶ ሥራ ባይሠራ ኖሮ የቡና ልማቱ በሌላ የሚተካበት ሁኔታ ይፈጠርም ነበር። ምክንያቱም ለውጥ ከመደረጉ በፊት በነበረው የቡና ልማት ይገኝ የነበረው የምርት መጠን ለመቀጠል የሚያስችል ስላልነበር ነው።

አሁን ላይ ኩባንያው የሚያለማው ቡና በአቅራቢያው ካሉ ቡና አልሚዎች ጋር ሲወዳደር ውጤታማነቱ ለንጽጽር የሚቀርብ አይደለም። ለቡና ተስማሚ የሚባሉ ሎውላንድ አካባቢዎች እንደ ሊሙ አካባቢ ያሉ ቡና አልሚዎችን ጭምር መቅደም ችሏል። ቀደም ሲል ግን በበቃ እርሻ ድርጅት ለሠራተኞቹ ደመወዝ ለመክፈል እንኳን ተቸግሮ ነበር። ሊሙ አካባቢ ቡና ከሚያለሙ ድርጅቶች ብድር እስከመውሰድ ደርሶ ነበር። ለሠራተኞቹ አነስተኛ ደሞዝ የሚከፍለውም በበቃ ቡና እርሻ ልማት ነበር። አሁን ላይ ግን የተገላቢጦሽ ነው የሆነው። በበቃ የለውጥ ጎዳና ላይ ነው። በእውቀት ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አድርጎ ለውጥ አምጥቷል።

**አዲስ ዘመን፤ ኩባንያው ምርታማነትን ለማሳደግ በገንዘብም በእውቀትም የታገዘ ሥራ መሥራቱን ገልጸውልናል። በሰው ኃይልም ሆነ በካፒታል ያለውን አደረጃጀት እንዲሁም ለአካባቢው የተፈጠረውን የሥራ ዕድል በተመለከተ ቢገልጹልን?**

**አቶ ሁነኛው፤** ኩባንያው ምርታማነቱን ለማሳደግ የተሻለ የቡና ዝርያ ለማግኘት የደከመውን ያህል አምራች የሆነ የሰው ኃይል ለማፍራትም ጥረት አድርጓል። በእርሻው፣ በሰው ኃይል አስተዳደሩም፣ በፋይናንሱም በሁሉም ዘርፎች በእውቀት የተደራጀ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። እዚህ ላይ መግለጽ የምፈልገው ኩባንያው እርሻ ልማቱን ሲረከብ የነበረውን የሰው ኃይልም አንድ ላይ ነው ያስቀጠልነው። እኔም ስለነበርኩ ምስክር መሆን እችላለሁ።

የሰው ኃይሉን በእውቀት የማብቃት ሥራ ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቱን የመሙላት ሥራ ነው የተሠራው። ጤናማ የሥራ መንፈስ ለመፍጠር አመለካከት ላይም ተሠርቷል። ለድርጅቱ ቀጣይነት የሰው ኃይሉ ላይ መሥራት አስፈላጊም በመሆኑ ኩባንያው ትኩረት ሰጥቷል። ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው ሠራተኛ የአካባቢው ነዋሪ ነው።

የሰው ኃይሉን በተመለከተም አሁን ላይ ቋሚ ሠራተኞች ከሁለት ሺ በላይ ናቸው። ወቅታዊ ሥራዎች ሲኖሩ ደግሞ ከስድስት ሺ እስከ ሰባት ሺ ጊዜያዊ ሠራተኞች ይቀጠራሉ። ጊዜያዊ ሠራተኞች ቁርጥ ሥራ በሚባል የአሠራር ዘዴ ስለሚሠሩ ሌላ ቦታም ተጨማሪ ሥራ መሥራት ዕድሉ አላቸው። በቡና ለቀማ ወቅት ግን የሰው ኃይሉ እስከ 11ሺ ይደርሳል። ኩባንያው በተቃራኒው የሰው ኃይል እጥረት ነው የሚያጋጥመው። ከፍተኛ የሰው ኃይል በሚያስፈልገበት ወቅት ሠራተኛ ለማግኘት ያስቸግራል።

**አዲስ ዘመን፤ ቡና መቼ እንደሚለቀም፣ በዓመት ምን ያህል ምርት እንደሚገኝና ተከላውንም አያይዘው ቢገልጹልን?**

**አቶ ሁነኛው፤** ቡና አብቦ ለፍሬ ለመብቃት እስከ ዘጠኝ ወር ጊዜ ይወስድበታል። በዚህ ሁኔታ ቡና በዓመት አንድ ዙር ለቀማ ይከናወናል ማለት ነው። አንድ የቡና ዛፍ በተለያየ ጊዜ ስለሚያብብ የለቀማ ጊዜው ከሦስት እስከ አራት ወራት ጊዜ ይወስዳል። በአማካይ ከ45ሺ እስከ 60ሺ ኩንታል ይገኛል። በያዝነው በጀት ዓመት ግን 166ሺ ኩንታል ቡና ተለቅሟል። ይሄ ከፍተኛው ነው። ከሚሰበሰበው ቡና 95 በመቶ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው። በእሸቱ ተለቅሞ እና ታጥቦ ነው የሚዘጋጀው።

በእርሻ ልማቱ ከቡና ልማቱ ጎን ለጎን የቁንዶ በርበሬ እና የእርድ ቅመም ይለማል። ቁንዶበርበሬ ከሦስት እስከ አምስት ሄክታር መሬት ላይ፣ እርድም ተመሳሳይ በሆነ ሄክታር መሬት ላይ ነው የሚለማው። ዓመታዊ ሰብል ውስጥ ነው የሚመደቡት። ቁንዶበርበሬ ቅመም ለለቀማ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ቡና ሲነሳ በበቃ እርሻ ልማት ድርጅትም...

ከገጽ 9 የዞረ

ሲደርስ ለቅሞ ለመጨረስ እስከ ሁለት ወር ጊዜ፣ እርድ ደግሞ እስከ አንድ ወር ጊዜ ይወስዳል። 180 ሄክታር መሬት ላይ የሚለማውን በቆሎም እንዲሁ ምርቱ ሲደርስ ይሰበሰባል። ልማቱ በዚህ መልኩ እየተከናወነ በመሆኑ በበቃ ላይ ዓመቱን ሙሉ ሥራ አይቋረጥም።

**አዲስ ዘመን፤ በኩባንያውና በሠራተኞች መካከል የተለያዩ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በምን መልኩ እንደሚፈታ፣ የቀን ሠራተኞች የሚያነሱት የክፍያ ማነስ ጥያቄ፣ የሠራተኛ ማኅበር ማቋቋም ጋር ተያይዞ ያለውንም ቢገልጹልን?**

**አቶ ሁነኛው፤**- ሠራተኞች መብትና ግዴታቸውን ለመወጣት እንዲያስችላቸው ማኅበር አቋቁመዋል። ማኅበሩ ከተቋቋመ ረጅም ጊዜው ነው። መሠረታዊ በሆነ ነገር ላይ መግባባት መኖር አለበት። ሠራተኛው የሚኖረው ድርጅቱ ዘላቂነት ሲኖረው ነው። ድርጅቱም ቀጣይነት የሚኖረው ሠራተኛው ሠላማዊ ሆኖ ሥራውን መሥራት ሲችል ነው። በዚህ ላይ አስተዳደሩም ሆነ የሠራተኛው ተወካይ የጋራ ግንዛቤ አላቸው። ይህንን መሠረት ያደረገ የኅብረት ስምምነት ያወጣሉ። ዳኛ ሆኖ የሚያገለግለውም የጋራ ስምምነቱ ነው። ይህ ሲባል ግን የመብት መጣስ የለም፣ ፍጹም ነው የሚል ድምዳሜ ላይ አንደርስም። ሠራተኞች የተለያዩ ጥያቄዎችና ቅሬታ ይኖራቸዋል።

መብቴ ተጥሷል የሚል ሠራተኛ ካለ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። በተቀመጠው የቅሬታ አፈታት መሠረት ይታይለታል። ችግሩ በደረጃ እስከ ሠራተኛ ማኅበሩ ድረስ ደርሶ የሚፈታበት አግባብ ስላለ ሠራተኛው መፍትሔ ያገኛል። በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል መፋጨቶች የሚኖረው የኅብረት ስምምነትን ለማምጣት ነው። ሌላው በድርጅቱ በኩል ለሠራተኛው ከሚያሟላቸው አንዱ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ነው። ሠራተኛው እየተጠቀመባቸው ያሉ መኖሪያ ቤቶች ከተገነቡ ረጅም ጊዜ ሆኗቸዋል። መታደስ ይኖርባቸዋል። ጊዜ የወሰደ ቢሆንም ደረጃ በደረጃ እድሳቱን ለማከናወን በእቅድ ተይዟል።

የቀን ሠራተኛን በተመለከተ ቅሬታ ውስጥ የሚከት ነገር የለም። የቀን ሠራተኛ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚሠራውንም የሚያገኘውንም ገቢ ቀድሞ ያውቃል። ኩባንያውም ቀድሞ በማስታወቂያ ስለሚያሳውቅ ተስማምቶ ነው ሥራውን የሚጀምረው። ቁርጥ ሥራ ነው የሚሠራው። መካድ የማይቻለው የቀን ሠራተኞች የክፍያ ማነስ ጥያቄ ያነሳሉ። ይህም ሆኖ በስምምነት ነው የሚሠራው። ግን ድርጅቱ መሸከም በሚችለው መጠን ጥያቄውን ለመመለስ ጥረት እያደረገ ነው። ችግሩን ለመጋራት በየጊዜው ማሻሻያ ያደርጋል። ምናልባት ፍላጎት ላይሟላ ይችላል።

**አዲስ ዘመን፤ ኩባንያዎች የአካባቢ ማኅበረሰብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማት ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አንፃር ኩባንያው የሠራው ሥራ ካለ ቢያብራሩልን?**

**አቶ ሁነኛው፤** አንዳንድ ክፍተቶች ነበሩ። አንዱ ክፍተት ኩባንያው የሚያከናውናቸውን የልማት ሥራዎች ፋይዳ በውል ያለመረዳት ነው። ኩባንያው የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ሊያግዝ እንደሚችልና ሌሎችንም አስፈላጊ ነገሮች ተመካክሮና ተወያይቶ ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ዕድሎች መኖራቸውን ባለመገንዘብ ድንበር የማበጀት ሁኔታ ነበር።

ኩባንያው ድርጅት ሆኖ እንዲቀጥል የአካባቢው ማኅበረሰብን መያዝ እንዳለበት እምነት ስላለው የነበረውን ክፍተት ከመቅረፍ ጀምሮ ነው የተንቀሳቀሰው። በዚህም ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጀምሮ በየእርከኑ ካሉ አመራሮች ጋር ጭምር ጤናማ የሆነ ግንኙነትና መቀራረብ መፍጠር ተችሏል። በሂደትም የኩባንያው አስፈላጊነት ጥሩ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል። ነገሮች በዚህ መልኩ ከተስተካከሉ በኋላ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል።

በልማት በኩል የመንገድ ሥራ ይገኝበታል። የእርሻ ልማቱ በሰባት አቅጣጫ ይዋሰናል። አዋሳኝ በሆኑ ሰባት ቀበሌዎች መንደር ከመንደር፣ እንዲሁም ቀበሌን ከቀበሌ የሚያገናኙ የመንገድ መሠረተ ልማት ለመሥራት ጥረት ተደርጓል። ትምህርት ቤትን ጨምሮ የተለያዩ ግንባታዎች ሲከናወኑም ጥያቄዎች ስለሚቀርቡ በተቻለ መጠን ትብብር ይደረጋል።



የበበቃ ቡና እርሻ ልማት በከፊል፤

**በበቃ እርሻ ልማት በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው የተቋቋመው። በኩታገጠም በሰፊ የቡና ማሣ ላይ የቡና ልማት የሚካሄድበት አካባቢ ነው፡፡ ይህም በሀገራችን ብቻ ሳይሆን፤ በምሥራቅ አፍሪካም ተጠቃሽ ነው**

ሙያዊ እገዛ ላይ ትብብር ያደርጋል። በበቃ እርሻ ልማት አምስት ዐቢይ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በዐቢዮቹ ሥር ደግሞ ንዑስ ክፍሎች አሉት። በነዚህ አደረጃጀቶች ውስጥ የሚሠሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች አሉን። በነዚህ ባለሙያዎች አማካኝነት ነው ለአካባቢው አርሶአደሮች ድጋፍ እያደረግን የምንገኘው። የቡና ችግኝም ሲፈልጉ ከወረዳዎች ጋር በመሆን ነው ስርጭቱ እንዲከናወን የምናደርገው። በቅርቡ የሚለቀቁ ምርታማ የሆኑ የቡና ችግኞችን ለወረዳ ለመስጠትም ታቅዷል። ለአካባቢው ማኅበረሰብ እየተደረገ ያለውን ድጋፍ እኛ ከምንናገር እራሳቸው ቢገልጹ የሚሻል ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፤ ቡና አረንጓዴው ወርቅ የሚል መጠሪያ የተሰጠው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደሆነ ይታወቃልና ከዚህ አንጻር በበቃ እርሻ ልማት በሀገር ምጣኔያዊ እድገት ላይ ያበረከተው አስተዋፅዖ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ሁነኛው፤** በበቃ እርሻ ልማት ድርጅት ትልቅ ትምህርት ቤት ሆኖ አገልግሎት የሰጠ የሀገር ባለውለታ ነው። አስተዋፅዖው የሚገለፀው ምርቱን ገበያ ላይ አውሎ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሀገር ኢኮኖሚው ላይ ባለው ፋይዳ ብቻ አይደለም። በቡናው ዘርፍ ትላልቅ የሚባሉ ባለሙያዎችንም አፍርቷል። በግላቸው በቡና ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት እያበረከቱ ካሉ ባለሀብቶች የወጡት ከበበቃ እርሻ ልማት ነው። ትላልቅ ኩባንያዎችን በኃላፊነት የሚመሩ ባለሙያዎችንም አፍርቷል።

የውጭ ምንዛሪን ለሀገር ከማስገኘት አኳያም ሚናው የላቀ ነው። ከሚያመርተው ቡና 95 በመቶው ለውጭ ገበያ እያቀረበ መሆኑ በቀላል የሚወሰድ አይደለም። ከፍተኛ እመርታ ነው። ለቡና ልማት ተስማሚ የሆነ የአየር ፀባይ የለም በሚባልበት አካባቢ ላይ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለውጥ በማምጣት ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግም በራሱ የተቋሙን ጥንካሬ ነው የሚያሳየው። የሀገር ባለውለታነቱንም ነው የሚያረጋግጠው። በጥራትና በብዛት ማምረት እንዲቻልም እንደሀገርም የመጀመሪያ የሆነ ዘመናዊ የምርት ማዘጋጃ ተቋም ገንብቶ አገልግሎት ላይ አውሏል።

**አዲስ ዘመን፤ እርሻ ልማቱ ውስጥ አሁን ላይ በመከናወን ላይ ከሚገኙ የልማት ሥራዎች በተጨማሪ ሌሎች ልማቶችን የማከናወን እቅድ አለ?**

**አቶ ሁነኛው፤** -አዎ እቅድ አለው። ዋናው ልማት ቡና ይሁን እንጂ ሌሎች ሰብሎች አሉ። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተለይም ዝቅተኛ በሚባለው አካባቢ ላይ ቅመማ ቅመም በስፋት ሊመረቱባቸው ይችላሉ። በዚሁ በኩልም እየሄድንበት ነው። ቁንዶ በርበሬ የቅመም ንጉሥ ተብሎ ነው የሚጠራው። በመሆኑም በገበያ ላይ በዋጋ ውድ ነው። የእርድ ቅመምም እንዲሁ በገበያ ላይ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው።

ለመኪና ጎማ ጥሬ እቃ የሚውል ተክል ለማልማትም ጥረት እየተደረገ ነው። ተክሉ በዋናነት ለጎማ ጥሬ እቃነት የሚያገለግል ቢሆንም ለሌሎች ግብዓቶችም ይውላል። አሁን ላይ በአነስተኛ መሬት ላይ እየለማ ነው። ካካዎ የተባለውን ተክልም ለማልማት ታስቧል። ወደፊት ልማቱን ማስፋት ይቻላል። በእቅድ ውስጥም ተካቷል። በአጠቃላይ ሁለገብ የልማት ሥራ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፤ በቆይታችን ያላነሳናቸውና ሲነሱ ይገባቸዋል የሚሉት ካለና በተለይ ደግሞ በድርጅቱ በኩልም ሆነ በሌላ አካል መስተካከል ያለባቸው ነገሮች ካሉ ቢያነሱልንና በዚሁ ብናጠቃልል?**

**አቶ ሁነኛው፤** ድርጅቱ ሰፊ እንደመሆኑ በእኔ እምነት ለአካባቢው እንደዓይን ብሌን የሚታይ ነው ። ይሄን ለማለት ያስቻለኝ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ያለው ሁሉ ለልማት ድርጅቱ እያደረጉ ያለው ድጋፍ ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ማኅበረሰቡ በየደረጃው ያለው አመራር ለልማት ድርጅቱ ጥበቃ ባያደርጉ ይህ ግዙፍ ድርጅት ምርታማነቱ ዘላቂ አይሆንም ነበር። ለወደፊትም ሰፊ እቅድ አያቅድም ነበር። የፀጥታ መደፍረስም ሆነ የተለያየ ችግር ሲኖር ፈጥኖ በመድረስ እያደረጉ ያለው ትብብር እንዲቀጥልና እገዛቸው እንዳይለየን ብዬ ነው የምጠይቀው።

ድጋፍና ክትትል በመኖሩ አልፎ አልፎም ቢሆን አካባቢው ላይ በነበረው የፀጥታ መደፍረስ የልማት ድርጅቱ ላይ ይህ ነው የሚባል ተፅዕኖ አላጋጠመውም። የፀጥታ መደፍረስ በአንዳንድ አካባቢ የሚገኙ የልማት ድርጅቶች እንቅስቃሴያቸው መገታቱን፣ ሀብትና ንብረታቸውም መውደሙንና ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጋቸውን እንሰማለን። በበቃ ቡና እርሻ ልማት ድርጅት ግን እንዲህ ያለው ፈተና አልገጠመውም። ይሄ በመልካም ጎኑ የሚገለጽ ነገር ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ እጅግ በጣም እናመሰግናለን።**

**አቶ ሁነኛው፤** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ፋሽን

## ስካርፎችን በሀገር ውስጥ

**ሰሚራ በርሀ**



በሀገራችን አንገት ላይ ጣል የምናደርገው ስካርፍ አልያም ሻርፕ በተለይ በቅዝቃዜ ወቅት በስፋት ጥቅም ሲውል ይስተዋላል። በሌሎች ሀገራት ደግሞ ከዚህም ባለፈ ለማጌጫነት የሚውልበት ሁኔታም አለ። ይህ ልብስ በተለያየ ብራንድ ለገበያ ይቀርባል ።

በዛሬው የፋሽን ገጻችንም ይህን ስካርፍ በተለያዩ ዲዛይኖች በማምረት ለገበያ ከምታቀርበው ዲዛይነር ቤዛዊት ዳንኤል ጋር ቆይታ አርገናል። ዲዛይነሯ የሀገራችንን ባሕል ሊያንጸባርቁ የሚችሉ ዲዛይኖች ያሏቸው ስካርፎችን ለገበያ በማቅረብ ትታወቃለች። ካሎን ዲዛይን የሚባል ድርጅት አላት፤ የድርጅቱም መሥራች እሷው ናት። በዚህ ድርጅቷ በተለያዩ ጨርቆች ላይ ዲዛይኖችን በማድረግ የምታመርታቸው ስካርፎች ተፈላጊት እንዳላቸውም ትናገራለች።

ቤዛዊት ስለድርጅቱ ስያሜ ስታብራራ ‹‹ካሎን›› የሚለው ቃል የግሪክ ቃል መሆኑን ጠቅሳ፣ ትርጓሜውም ውበት የሚል ነው ትላለች። ‹‹መጽሐፍት በማነብበት ወቅት ያገኘሁት ቃል ነው፤ ወደእዚህ ሥራ ስገባ ይህንን ቃል ለመምረጥ የቻልኩትም ለእዚህ ነው›› ትላለች ።

‹‹ካሎን ዲዛይን ከስካርፎች ባለፈ የተለያዩ ጌጣጌጦችን በተለያዩ ዲዛይኖች ይዞ ይወጣል። ለእሷ ፋሽን ማለት አለባበስ አልያም መዘነጥ ብቻ አይደለም። ‹‹የአኗኗር ዘዴያችንን ጭምር የምናንፀባርቅበት ነው›› ትላለች።

ቤዛዊት ከልጅነቷ አንስቶ ፍላጎቷ አርክቴክት መሆን ነበር። በዚሁ መሠረትም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስትገባ የአርክቴክት ሙያ መማርን ምርጫዋ አድርጋለች። በዚህም ትምህርቷን አጠናቃለች። የምትሠራው ፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ ይሁን እንጂ የአርክቴክት ሙያዋን የምታንፀባርቅበት አርጋዋለች።

ቤዛዊት ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ በተማረችበት ሙያ ለመሥራት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አድርጋለች። ከዚያም የቤተሰቦቿ ቢዝነስ ወደሆነው የጨርቃጨርቅ ሥራ ውስጥ በመግባት የመሥራት ዕድሉም አግኝታለች። በእነዚህ ጊዜያት ግን በአካባቢዋ የምትመለከተውን እንቅስቃሴ በውስጧ የሚሰማትን ሁሉ በስዕል መልክ ታሰፍርም ነበር ።

እነዚህን ስዕሎች በጨርቆች ላይ ማስፈር እና ወደ ስካርፍ መቀየር የሚለው ሀሳብ እንዴት እንደመጣላት ስትገልጽም፤ በአንድ ወቅት አንድ ኤግዚቢሽን ላይ የክቡር ዶክተር ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ስዕሎች በስካርፎች ላይ ተሠርተው መመልከቷን አስታወሰች። ከዚህም እንደዚህም መሠራት ይችላል የሚለውን ሀሳብ ማግኘቷን ቻለች። ቤዛዊት የክቡር ዶክተር ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የስዕል ሥራዎች አድናቂ ናት።

የስዕል ሥራዎቿን ‹‹ሲልክ›› የሚባለውን የጨርቅ አይነት በመጠቀም በኅትመት መልክ እንዲሠሩ አደረገች። ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠራው ስካርፍም በሰዎች ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት አገኘላት።

ቤዛዊቲ አሁን ላይ ከ25 በላይ የሚሆኑ በስካርፍ ላይ የሠራቻቸው የራሷ ዲዛይኖች እንዳሏት ጠቅሳ፣ ስካርፉን ለመሥራት የምትጠቀመው የጨርቅ ግብዓት ከውጭ እንደሚመጣ ተናግራለች። ይህ ከባድ አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ አቅርበንላት ነበር። ‹‹ይከብዳል፤ ነገር ግን ሁሉም ሥራ የራሱ ፈተና አለው፤ ከችግሩ ይልቅ መፍትሔው ላይ ማተኮር የተሻለ ነው›› በማለት መልሳልናለች።

በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ከሚወጡ ጨርቆች ይልቅ እነዚህን ጨርቆች ለመቀበል የተገደደችው ምርቶቹን በምትፈልገው መጠን እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማግኘት ባለመቻሏ መሆኑን አስታውቃለች። አሁን ካሎን ዲዛይን ከሚሠራቸው ሥራዎች እነዚህን በሀገር ውስጥ የሚሠሩ ስካርፎች ወደ መሥራት ሙሉ ለሙሉ ተሸጋግሯል ስትል ጠቅሳ፣ ዲዛይኖቹም ሙሉ ለሙሉ የዲዛይነር ቤዛዊት መሆናቸውን ተናግራለች።

እነዚህን ዲዛይኖች ከማቅረብ ውጪ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን እንደምትሠራ ተናግራ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር ስትሠራ የተቋማቱን ሎጎ እና ዓላማ በሚገልጽ መልኩ ዲዛይኖች እንደሚሠሩ ቤዛዊት ትገልጻለች ።

እሷ እንዳለችው፤ በካሎን ዲዛይን የሚሠሩ የስካርፍ ዲዛይኖች በኢትዮጵያ ያልተለመዱ ሲሆኑ፣ ምኑ ኢትዮጵያዊ ያስብላቸዋል? ምን መልዕክትስ ያስተላልፋሉ? ብለን ላቀረብንላት ጥያቄ ቤዛዊት ስትመልስ ‹‹በአካባቢዬ የማየውን ነገር ማስተዋል ላይ ጥሩ ነኝ ብዬ አስባለሁ፤ ዲዛይኖቼም የማየውንና የውስጤን ሀሳብ የሚያንጸባርቁ ናቸው ብዬ አምናለሁ። ሀገራችንን የሚገልጹ ለምሳሌ የራሳችንን ፊደላት የግዕዝ ቁጥሮች፣ ቆየት ያሉ የኢትዮጵያውያን የሆኑ ዲዛይኖችን እጠቀማለሁ ›› በማለት ትገልጻለች።

የካሎን ዲዛይን ሥራዎች በሌሎች ሀገር ዜጎች ጭምር ተወዳጅ ናቸው የምትለው ቤዛዊት፣ ከምትሠራቸው ሀገራዊ ገጽታ ካላቸው ዲዛይኖች ባሻገር አብስትራክት የሆኑ እና ለዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የሚሆኑ ዲዛይኖችንም ትሠራለች ።

የካሎን ዲዛይን ስካርፎች ባላቸው ቀለም፣ መጠን እና ዲዛይን በይበልጥ ሰዎች አለባበሳቸውን በተለየ መልኩ ለማስዋብ ስታይል ለማድረግ ከአለባበሳቸው በተጨማሪ ውበትን ለማከል ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉም ተናግራ፣ ለየትኛውም ወቅትና ቦታ የሚለበሱ መሆናቸውንም አመልክታለች።

ቤዛዊት እነዚህን ሥራዎቿን በተለያዩ የማኅበራዊ ገጾች ላይ ታስተዋውቃለች። ይህም ሥራዋን ለማስተዋወቅ እንዲሁም ብዙዎች ዘንድ ለመድረስ ጠቅሟታል። የምትሠራቸው ሥራዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ለኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ክብርት ሣሕለወርቅ ዘውዴ እንዲሁም ለኬንያ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ባለቤት ቀዳማዊት እመቤት ራቼል ሩቶ ዘንድ መድረሳቸውንም አስታውቃለች።

‹‹የክብርት ፕሬዚዳንቷ የቅርብ ወዳጅ ከእኛ ወስደው በስጦታ መልክ ካበረከቱላቸው በኋላ ወደውት በተለያዩ ጊዜያት የስካርፋችን ተጠቃሚ ሆነዋል›› የምትለው ቤዛዊት፣ ይህ አጋጣሚ ለእሷ ትልቅ ዕድል እንደሆነ ጠቅሳለች ።

የካሎን ዲዛይን የስካርፍ ሥራዎች በሚቀጥሉት ዓመታት ኢትዮጵያ በዓለምአቀፍ ደረጃ ከምትታወቅባቸው ምርቶች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ቤዛዊት አቅዳ እየሠራች መሆኗንም አስታውቃለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የቡሄ ጨዋታ

**ዋስልኝ አየለ**

ዛሬ ቡሄ ነው። ‹‹እዚያ ማዶ ጭስ ይጨሳል...›› የሚለው የልጆች የሆያ ሆየ ዘፈን ይዘፈናል። በነገራችን ላይ ይሄ የልጆች የሆያ ሆየ ጭፈራ ውስጠ ወይራ ነው ይባላል። በድሮው ጊዜ የመገናኛ ብዙኃን አማራጭ አልነበረም። እረኞች በእንጉርጉሮ ስሜታቸውን ይገልጻሉ። ለዚህም ይመስላል በነገሥታቱ ዘመን ‹‹እረኛ ምን አለ?›› የሚል የዳሰሳ ጥናት ይደረግ ነበር ይባላል። የሕዝብን ስሜት ከእረኛ ይሰማሉ ማለት ነው። እረኞች ልጆች ስለሆኑ ከወላጆቻቸው የሚሰሙትን ያንፀባርቃሉ። ከእነዚህ የልጆች ሀሳብ ማንጸባረቂያ መድረኮች አንዱ ቡሄ ነው።

የዛሬው ቡሄ ልጆች በየመንደሩ እየዞሩ የሚጨፍሩበት (በተለይም ቀደም ባለው ዘመን) ነው። በስንኞቻቸው ያስደሰታቸውን የሚያወድሱበት፤ ያስከፋቸውን ሽንቆጥ የሚያደርጉበት ነው። እንዲህ አይነት ክስተቶች የዘመን ምስክር ናቸው። ያ ዘመን ምን ይመስል እንደነበር፤ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎችን ያሳያሉ።

ከልጆች የሚሰሙ ስንኞች የድሮ ቃል ግጥሞች ብቻ አይደሉም፤ በዘመኑ ዓውድ ቀይረው አሁን ያለውን ለመግለጽ የሚጠቀሟቸውም አሉ። ለምሳሌ፤ በኢሕአዴግ ጊዜ መንግሥት በተደጋጋሚ ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› ሲል ይሰማል። ይሄው ክስተት በልጆች ሆያ ሆየ ውስጥ ተካቶ ሲጨፈር ሰምተናል። ‹‹እረኛ ምን አለ? ማለት ይሄው ነው።

እንዲህ አይነት ቱባ የማኅበረሰብ የኪነ ጥበብ ውጤቶች ብዙም ሽፋን አያገኙም። ማኅበረሰብን ለማወቅ ግን ትክክለኛው መገለጫ ይሄው ነበር። በነገራችን ላይ የሠለጠኑ ናቸው በሚባሉት ሀገራት የተሠራ አንድ ጥናት አንብቤ ነበር። ጥናቱ የሥነ ማኅበረሰብ (ሶሾዮሎጂ) ጥናት ነው። አጥኚው አጠናው የተባለው መጠይቅ እየበተነ አይደለም። የከተሞችን የሌሊት ሕይወት (Nightlife) በማጥናት ነው። እንደ ለንደን፣ ፓሪስ፣ በርሊን.... የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ከተሞች የምሽትና የሌሊት እንቅስቃሴዎቻቸው ይቀረጻል። ትክክለኛውን ማንነት ማየት የሚቻለው በዚህ ነው ማለት ነው።

የእረኞችና የልጆች ጨዋታም እንደዚህ ነው። በራሳቸው ስሜት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ማለት ነው። ስለዚህ የዘርፉ ሰዎች ልብ እንዲሉት (እንዲያጠኑት) እየጠቆምን እስኪ አንዳንድ የቡሄ የጨዋታ ስንኞችን እናስታውስ።

**ቡሄ መጣ**
**ያ መሳጣ**
**ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ**

ይሄ ከቃሉ ትርጉም ጋር የሚሄድ ነው። ‹‹ቡሄ›› ማለት ቡሃ ከሚለው ቃል የመጣ ነው፤ ቡሃ ማለት ገላጣ ማለት መሆኑን የሃይማኖት አባቶችና የቋንቋ ሰዎች በየዓመቱ ይናገሩታል።

**የእኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት**
**ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት**
**መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት**

ይሄ የውደሳ ግጥም ነው። በድሮው ጊዜ ለሆያ ሆያ ልጆች ሙክት (ፍየል) ይሰጥ ነበር ማለት ነው። በነገራችን ላይ በገጠር አካባቢ ልጆች ከሆያ ሆየ የሚያገኙትን ብር ሙክት ገዝተው ነው የሚበሉበት። የቅጠል ድንኳን (ዳስ) ይሠራል። ከአካባቢው ሰዎች ይገባቸዋል ያሏቸውን (ሽማግሌና የሃይማኖት አባት) ይጠራሉ። ከዚያ ውጭ የመጣ ግን ቀላዋጭ ነውና የሚጠብቀው የልጆች ግልምጫና ውረፋ ነው።

ሆያ ሆየ ሲሉ ብር የሚቀበሉት እንደየሰዎች አቅም ነው። የአካባቢው ልጆች ስለሆኑ የየሰውን አቅም ያውቁታል። ሀብታም ከሆነ በቀላል አይላቀቁም። ‹‹ከአንተ ይሄን አንቀበልም›› ብለው ሆያ ሆየውን ይደጋግሙታል። ከእንዲህ አይነቱ ሀብታም ነው ሙክት የተበረከተላቸው ማለት ነው። ‹‹መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት›› ማለት ከቀናት በኋላ የሚገባውን መስከረም ሳይሆን በዓመቱ የሚመጣውን ነው።

**የእኔማ እመቤት የፈተለችው**
**የሸረሪት ድር አስመሰለችው**
**ሸማኔ አቅቶት ማርያም ሠራችው**

ይሄም ውደሳ ነው። ይሄኛው ውደሳ ለእመቤቷ ነው። በዘመኑ የሴት ሙያ የሚለካው በፈታይነትና በባልትና ብቃት ነው።

ከድሮው የቃል ግጥም እንውጣና በቅርቡ ዘመን የተባሉትን ደግሞ እንያቸው። በዘመኑ የሚታየውን፣ የሚባለውን፣ የሚሆነውን የሚናገሩ ናቸው። ያም ሆኖ ግን መነሻ ስንኞቻቸው የቀደሞቹ ናቸው።

**ወዲያ ማዶ አንድ ጋቢ**
**ወዲህ ማዶ አንድ ጋቢ**
**የኔማ እንትና ኪራይ ሰብሳቢ!**

ምናልባት ይሄ በተባለበት ጊዜ ጭስ አልነበረም መሰለኝ በጋቢ ቀይረውታል። ኪራይ ሰብሳቢ የሚለውን ለመግለጽ ቤት እንዲመታላቸው ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹ጭስ›› ካሉ ሙሉ በሙሉ የድሮው ሊሆን ነው። ያስከፋቸውን ሰው ኪራይ ሰብሳቢ ብለው ሲሰድቡት ያስደሰታቸውን ደግሞ እንዲህ ብለዋል።

**እዛ ማዶ አንድ በረኪና**
**እዚህ ማዶ አንድ በረኪና**
**የኔማ አባብዬ ባለመኪና**

እዚህ ጋ የተቀየረው ሌላው ነገር ‹‹ጌታ›› የሚለው ነው። በድሮው ጊዜ ጌታ እና እመቤት የሚሉ ቃላት ነበሩ፤ አሁን አባዬ እና እማዝየ በሚል መሆኑ ነው። ለዚህም ነው ለሴቷ እንዲህ የተባለው።

**እዛ ማዶ አሮጌ ትሪ**
**እዚህ ማዶ አሮጌ ትሪ**
**የእኔማ እማምዬ ማሪያ ኬሪ**

ግን ‹‹አዲስ ትሪ›› ቢሉት ምን ችግር ነበረው? ወይስ አሮጌው ትሪ ያልገባኝ መልዕክት ይኖረው ይሆን? እንዲያውም ከማሪያ ኬሪ ጋር የሚሄድ አዲስ ትሪ ቢሆን ነበር (ለነገሩ ማሪያ ኬሪም እያረጀች ነው)። ችግሩ ዘፋኝም ተዋናይም የራሳችን እያሉን የውጭዋን ማስበለጣቸው ነው።

**ተው ስጠኝና ልሂድልህ**
**እንደ አሮጌ ጅብ አልጨህብህ**

የልጆችና የእረኞች ቃል ግጥሞች የአዋቂዎች እጅ ያለበት ይመስላል። እርግጥ ነው ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ነው፤ ግን ጨዋታው የልጆች ብቻ ስለሆነ ከልጅ ወደ ልጅ እንጂ ከአዋቂዎች ወደ ልጅ ይተላለፋል? ወይስ ነገር ስለምናጣምም እነርሱ ያላሰቡትን ትርጉም እየሰጠነው ይሆን? አይመስለኝም! ‹‹ያለአንድ ሰው አታስተኛ›› የተባለው መቼም የሆያ ሆየ ጎረምሳ ከአባወራ ቤት አልጋ ላይ ይተኛል ተብሎ አይደለም። የጌቶች ወንበር በቀላሉ አይገኝም ለማለት ነው።

**እዚያ ማዶ ጭስ ይጨሳል**
**አጋፋሪ ይደግሳል**
**ይሄን ድግስ ውጩ ውጩ**
**ከድንክ አልጋ ተገልብጩ**
**ያቺ ድንክ አልጋ ነገረኛ**
**ያለአንድ ሰው አታስተኛ!**

# ዓለም አቀፍ



## ጀርመን ለዩክሬን የምትሰጠውን ድጋፍ እንደምታቆም ገለጸች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ጀርመን ለዩክሬን የምትሰጠውን ድጋፍ እንደምታቆም ገለጸች፡፡

ሶስተኛ ዓመቱ ላይ የሚገኘው የሩሲያ- ዩክሬን ጦርነት እንደቀጠለ ሲሆን፤ ጀርመንን ጨምሮ ምዕራባዊያን ሀገራት ለዩክሬን ገንዘብን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

ዩክሬን ከሩሲያ የሚሰነዘርባትን ጥቃት ለመመከት ድጋፍ ከሚያደርጉላት ሀገራት መካከል ጀርመን ዋነኛዋ ስትሆን ከ2025 ጀምሮ ድጋፏን እንደምታቆም አስታውቃለች፡፡

ጀርመን ለዩክሬን የምትሰጠውን ድጋፍ የምታቆመው ሀገሪቱ ያለባት የብድር ጫና እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት እንደሆነ ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

አሜሪካ ለዩክሬን ከፍተኛ ገንዘብ እና የጦር መሳሪያዎችን ለዩክሬን ድጋፍ ከሚያደርጉ ሀገራት መካከል ቀዳሚዋ ስትሆን ጀርመን በሁለተኝነት ላይ ተቀምጣለች።

ጀርመን በተያዘው የፈረንጆቹ 2024 ዓመት ውስጥ ብቻ ለዩክሬን ስምንት ቢሊዮን ዩሮ ድጋፍ ማድረጓ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ጀርመንን ጨምሮ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት 300 ቢሊዮን ዩሮ የሩሲያ መንግሥት ሀብት እንዳይንቀሳቀስ የታገደ ሲሆን፤ ይህ ገንዘብ ለዩክሬን መልሶ ልማት እንዲውል ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡

በጀርመን ከታገደ የሩሲያ መንግሥት ሀብት ላይ በወለድ መልክ የሚገኘው 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዩሮ ለዩክሬን ድጋፍ እንደሚሰጥ የመራሄ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ መንግሥት አስታውቋል፡፡

በምርጫ ቅስቀሳ ላይ ያሉት ዶናልድ ትራምፕ ምርጫውን ካሸነፉ ለዩክሬን የሚደረገውን ድጋፍ እንደሚያቆሙ መናገራቸው አይዘነጋም፡፡

ትራምፕ አክለውም ፕሬዚዳንት ባይደን የአሜሪካዊያንን ገንዘብ ለዩክሬን በመስጠት ሀብት አባክኗል ሲሉ የወቀሱ ሲሆን፤ ስልጣን በያዙ ማግስት ጦርነቱን እንደሚያስቆሙ ቃል ገብተዋል፡፡



## የወሊድ መከላከያ ሕ ስ የወሰደው አባወራ ድጋሚ አባት መሆኑን ተከትሎ ክስ መሰረተ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአራት ልጆች አባት የሆነው ሰው እርግዝና እንዳይፈጠር የሚከላከል ሕክምና ቢያደርግም ሳይፈልግ አምስተኛ ልጅ አባት ለመሆን ተገዷል።

የሕክምና ስህተት የሰራው ተቋም ልጄ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ የማሳደጊያ ይከፈለኝ ሲል ክስ መስርቷል።

ማክሲም የተሰኘው ሩሲያዊ የ45 ዓመት አባወራ ሲሆን፤ የአራት ልጆች አባትም ነው፡፡ የኢኮኖሚ እና ሌሎች አቅሙን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከባለቤቱ ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ተጨማሪ ልጆችን ላለመውለድ ይወስናሉ፡፡

ዘላቂ የወሊድ መከላከያ ለመውሰድ የተስማሙት እነዚህ ወላጆች አባትየው እርግዝና እንዲፈጠር የሚያደርገውን ወይም የዘር ፍሬ ቱቦ በማስቆረጥ ወይም በእንግሊዘኛው ቫስክቶሚ የተሰኘውን ሕክምና ያደርጋል።

በዘር ፍሬ ቱቦው ላይ ባደረገው የቀዶ ህክምና አማካኝነት ልጅ መውለድ እንደማይችል የተነገረው ይህ ሰውም ባለቤቱ አምስተኛ ልጅ እርጉዝ መሆኗን ትነግረዋለች፡፡

በውጤቱ የተጠራጠረው ይህ ሰውም ድጋሚ ባደረገው ምርመራ አምስተኛ ልጅ አባት ለመሆን የተገደደ ሲሆን፤ ህክምናውን ባደረገለት ክሊኒክ ላይ ክስ መስርቷል፡፡

ቀዶ ህክምናውን ያደረገው ክሊኒክም የተፈጠረውን ነገር ማመን ባለመቻሉ በግለሰቡ ላይ ባደረገው ድጋሚ ምርመራ አሁንም ማስረገዝ እንደሚችል ያረጋግጣል፡፡

ክስ የተመሰረተበት ክሊኒክ ከደንበኛው ለቀዶ ህክምና የተቀበለውን ክፍያ መመለስ እንደሚችል ቢናገርም ግለሰቡ ከዚህ ያለፈ ካሳ እንደሚፈልግ ተናግሯል ተብሏል፡፡

ያለ ፍላጎቱ የአምስተኛ ልጅ አባት የሆነው ግለሰብ እኔ ሕክምናውን ያደረኩት ኢኮኖሚዬን እና የማሳደግ አቅሙን አይቶ እንደነበር እንዲሁም ክሊኒኩ በሰራው ስህተት ምክንያት ለተጨማሪ ጫናዎች መዳረጉን ተናግሯል፡፡

ግለሰቡ ለደረሱበት ጫናዎች ካሳ እንደሚፈልግ ቢናገርም፤ ክሊኒኩ ግን እኔ የሰራሁት ስህተት የለም ነገር ግን ግለሰቡ በተዓምር ነው አምስተኛ ልጅ ሊወልድ የቻለው በሚል ክርክሩ እንደቀጠለ ይገኛል ሲል ኦዲቲ ሴንትራል ዘግቧል፡፡

# ስፖርቱን ከውድቀት ሀገርን ከአንገት መድፋት እንታደግ !

መኮንን ይደርሳል

የሀገራችንን ስፖርት የገጠመው አንዱ ተግዳሮት የአሠራር ብልሽትና የሕዝባዊ አደረጃጀቱ የአመራር ችግር ነው። የስፖርት ማኅበራት ተጠቅልለው በተወሰኑ ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ገብተዋል። እነዚህ ግለሰቦች ሲተነፍሱ አብረው የሚተነፍሱ እነሱ ሲያቆሙ ደግሞ እስትንፋሳቸው አብሮ የሚያቆም ሆኗል። እነዚህ ግለሰቦች ደግሞ ከፋታቸው ብዙ ጊዜ የሚተነፍሱ አይደሉም።

በዚህም ምክንያት እ.ኤ.አ በ2016 ከተካሄደው የሪዮ ኦሊምፒክ ጀምሮ ሲያነክስ የመጣው የአትሌቲክስ ስፖርት ተንገራግጮ ሊቆም ግድ ብሎታል። በብልሹ አሠራርና በግለሰቦች የአመራር ችግር እግር ተወርቾ በመታሰሩ ከዚህ በላይ ሊንቀሳቀስ አልተቻለውም። በተወሰኑ አትሌቶችና አሠልጣኞች የግል ጥረት ሲወዛወዝ ቢቆይም የፓሪስ ኦሊምፒክን መሻገር ተስኖታል።

ሕግን የማይከተሉና የግለሰቦችን ጥቅም ብቻ ለማስከበር የሚነደፉ አሠራሮች ስፖርቱን አቀጭጨው እንዲዳከም አደረጉት። ከምንም በላይ ደግሞ ለጭቅጭቅና ለርስ በርስ አለመግባባት መንስኤ በመሆናቸው የስፖርቱን ገፅታ አበላሹት። ኦሊምፒክ የሠላም፣ የፍቅርና የአንድነት መድረክ መሆኑ ቀርቶ የንትርክና የመጠላላት ዋና መገለጫ እንዲሆን አስገደዱት።

የስፖርቱ የበላይ አመራር ነን የሚሉ ግለሰቦች የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ ብቻ ሕግ ቀየሩ ወይም አሻሻሉ። በሚያስደንቅ ሁኔታ ጠቅላላ ጉባኤ ተብየውም በዝግ ተሰብስቦ «ጌቶች ሆይ ሕጋችሁን አፅድቄያለሁ» የሚል አስገራሚ ምላሽ ሰጠ። ከዚህም በመነሳት ብዙ ዓለም አቀፍና የሀገራችንን ሕጎች ጥሶ የሥልጣን ጊዜያቸውን መርቆ ለሌላ የሥልጣን ዘመን አራዝሜያለሁ አለ። በምትኩም በአይነት፣ በገንዘብ እንዲሁም ኤፍል ታወር (Eiffel Tower) በሚደርስ የፓሪስ ሽርሽር ሽልማት ተበረከተለት። ምን አልባት በታሪክ የአንድ ተቋም (የኦሊምፒክ ኮሚቴ) ጠቅላላ ጉባኤ እና የፌዴሬሽን (የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የኦሊምፒክ ልዑክ ሆኖ ሲሄድ የመጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም። ሪከርድ ሆኖ መመዝገብም ይኖርበታል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤን ለምን እንደዘነጉትና በልዑኩ ውስጥ ሳያካትቱት እንደቀሩ ግን እስካሁን አልገባኝም። ለነገሩ በተለያየ መንገድ አብዛኛው ተካቷል መሰለኝ።

ከዚህ ባለፈ ከጠቅላላ ጉባኤው በተረፈው ቦታ ላይ እንኳን በኦሊምፒክ የሚሳተፉ አካላት የሚለዩበት ግልፅ መስፈርት እና አሠራር አልተቀመጠም። ወደ ቦታው ሲሄዱ የሚሠሩት ሥራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ለአመራሩ ቅርብና ባለውለታ የሆኑ ግለሰቦች ከዚህም አለፍ ሲል ዘመድ አዝማድ የሆኑት ብቻ ከያሉበት ተጠራርተው ጉዞ ወደ ፓሪስ አደረጉ። በሕዝብ ሀብት እንደዚህ ተቀለደ።

አሠራሩ ሁሉ ከጅምሩ አንስቶ እስከ መጨረሻው በብልሽት ታጀበ። ይህም በስፖርተኛው፣ በስፖርቱ ማኅበረሰብና በኢትዮጵያውያን ላይ ዳር እስከ ዳር ብስጭትን ቀሰቀሰ። የሁሉም ዓይን ወደ ፓሪስ እንዲሆን አደረገ።

የስፖርተኛው እንዲሁም ወደ ፓሪስ የሚሄደው ሚዲያና ጋዜጠኛ ምርጫም በተመሳሳይ መልኩ ሕግንና አሠራርን ያልተከተለና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የተከናወነ ባለመሆኑ ቅድመ ዝግጅቱንም ይሁን ውድድሩን እጅጉን አወከው። የዚህ ውጤትም ተወዳድሮ ከማሸነፍ ይልቅ መተራመስ ሆነ።

ከፓሪስ ቅድመ ዝግጅትና ውድድርም ባለፈ በተቋማቱ ያለው አሠራር እጅጉን ደካማ እንደሆነ ከብዙዎች ይደመጣል። አሳታፊ ያልሆነና የግለሰቦች አምባገነንነት ጎልቶ የሚንፀባረቅበት እንደሆነ በስፋት ይነሳል። ትልልቅ ጉዳዮች ሳይቀሩ በግል ይወሰናሉ፤ ይፈፀማሉ። ይህም ተጠያቂነት እንዳይኖርና ግለሰቦች እንደፈለጉ እንዲፈነጩ ዕድል ሰጥቷቸዋል። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤትም በከበርንበት የኦሊምፒክ መድረክ አንገት መድፋት ሆኗል።

> **በተለይ የቡድን መንፈስን የሚረብሹ ሂደቶችን በማስወገድ ግልፀኝነት የተሞላበት የስፖርት ተቋምና አሠራር ሊፈጠር ይገባል**

ሕዝባዊ የስፖርት ተቋማት ሀብት የሚያስተዳድሩበት፣ ዓለም አቀፍ ውድድር የሚመሩበት፣ አትሌት የሚመለምሉበት፣ የሰው ኃይላቸውን የሚያስተዳድሩበት፣ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሩበት ውስጣዊና ውጫዊ የአሠራር ሥርዓት የሌላቸው እንዲሁም ያለውንም የመተግበር ሞራል ያጡ በመሆናቸው መጨረሻው የሀገር ውጤት ውድቀት ሆነ። በመልካም አስተዳደር ችግር ስፖርቱን ከላይ እስከታች ናጡት። በታላቁ የኦሊምፒክ አደባባይ የሀገር ውጤት በማሳጣት የስፖርቱንም ገፅታ ክፉኛ ጎዱት። ሕዝባችንንም አሳዘኑ።

ከዳዴ አልወጣ ያለውና ሁልጊዜ ጨቅላ የሚሆነው የስፖርት ሕዝባዊ አደረጃጀት (የስፖርት ማኅበር) ከሌሎች ክፍተቶቻችን ጋር ተዳምሮ ለዓለም አቀፍ ውጤታችን መዳከምና ለስፖርቱ መቀጨጭ ትልቁ መንስኤ ሆነ።

የሀገራችን ስፖርት ፖሊሲ ስፖርቱ ሕዝባዊ እንዲሆንና ቀስ በቀስ ራሱን መቻል እንደሚጠበቅበት ግልፅ አቅጣጫ ያስቀምጣል። ይህም ማለት ስፖርቱን በሀገራችን በማስፋፋት ኅብረተሰቡ በብዛት እንዲያዘወትረው ማስቻልንና እገረ መንገዱን ደግሞ በተለያየ መንገድ (በክለብ፣ በኮሚቴ፣ በማኅበር ወይም ከዚያ ከፍ ባለ ደረጃ) ተደራጅቶ እንዲመራው እንዲሁም ስፖርቱን ማስተዳደር የሚያስችለውን ሃብት እንዲያመነጭ ማድረግን የሚመለከት ፅንሰ ኃሳብ ነው። በውጤቱም ሀገራችን ኢትዮጵያ እና ዜጎቿ እንደ ሌላው ዓለም ሁሉ ከኢንዱስትሪው ማግኘት የሚጠበቅባቸውን የጤና፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ማረጋገጥ እና በዓለም አቀፍ መድረክ ወጤት ማስመዝገብን ይመለከታል።

ይህን የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ላለፉት ሩብ ምዕተ ዓመታት (26 ዓመታት) ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ቢደረጉም የሚፈለገውን ያህል ለውጥ ማስመዝገብ አልተቻለም። በተቃራኒው የፖሊሲው ፅንሰ ኃሳብ እየተዛባ መጥቶ በስመ ማኅበር የተወሰኑ ግለሰቦች ሀብት ወደመሆን የተሸጋገሩና ምንም የተቋምነት ይዘትና ቅርፅ የሌላቸውን የስፖርት ድርጅቶች መፍጠር ላይ ሊወሰን ግድ ብሎታል።

በዚህ ሂደትም የስፖርቱ ሕዝባዊነት እየቀጨጨ መጥቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፌዴሬሽን ወይም የኮሚቴ ስያሜን የያዙ ነገር ግን የአንድ ወይም ሁለት ግለሰቦች አዛዥ ናዛዥነት ጎልቶ የሚስተዋልባቸውን ደካማ ድርጅቶች እውን ማድረግ የመጨረሻ ውጤቱ ሆነ። እነዚህ የስፖርት ድርጅቶችም (ተቋም ያላልኩት ሳይንሳዊ መስፈርቱን ስለማያሟሉ ነው) በፍጥነት የውስን ግለሰቦች የግል ሀብት (Property) ወደ መሆን ተሸጋገሩ።

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴን ጨምሮ አብዛኞቹ የታወቀ ተቋማዊ መዋቅር (Organizational Structure) ቀርፀው በግልፅ ማስታወቂያ የሰው ኃይል ቅጥርና ስምሪት ሲያከናውኑ አይታይም። ይህም ተቋማቱ በይፋ ኅብረተሰቡ የሚያውቀው ውስጣዊ አደረጃጀት የላቸውም አልያም ደግሞ በውስጥ ለውስጥ የዘመድ አዝማድ መሰባሰቢያ ሆነዋል የሚለው አንድምታ ላይ ያደርሳል።

ይህ ተቋማዊ አደረጃጀት ሠንሠለቱን ጠብቆ ከፌዴራል ወደ ክልል ከዚያም ወደ ክለብ እና ሌሎች መሰል መዋቅሮች እንዲወርድ ይጠበቃል። ነገር ግን በተሟላ መንገድ ሊሳካ አልቻለም። በሚያስገርም ሁኔታ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የክልል መንግሥታትን የስፖርት መዋቅር "የእኔ ቅርንጫፎች" የሚል ስያሜ ሲሰጣቸው ይስተዋላል። ይህ ፍፁም ስህተት ነው። የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አፈጣጠር ከሀገር አቀፍ የስፖርት ማኅበራት ስብስብ ብቻ እንደሚሆን ልብ ሊባል ይገባል።

በተመሳሳይ መልኩ ከተቋማዊ አደረጃጀት ባለፈ ከዓመት እስከ ዓመት አስፈላጊውን የስፖርት ልማታዊ እንቅስቃሴ መከወንም ይሁን ሥራ መሥራት የሚያስችል የሰው ኃይል የላቸውም። የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴን በምሳሌነት ወስደን ብንመለከት በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ቁጥራቸው 40 እንኳን የማይደርሱ ስፖርተኞችን በርከት ካሉ አጃቢዎች (የአመራሩ ቅርብ ሰዎች) ጋር ወደ ኦሊምፒክ መንደር ማድረስ ላይ ተወስኗል። ከዓመት እስከ ዓመት መሥራት የሚገባቸው የስፖርት ልማት እንቅስቃሴዎች እና የኦሊምፒክ ሶሊዳሪቲ ፕሮግራሞች በር ከተዘጋባቸው ሰነባብተዋል።

የስፖርት ድርጅቶቹ በየእርከኑ የመንግሥትን እጅ ከመመልከት ባለፈ ኅብረተሰቡን በማሳተፍ ተጨማሪ ሀብት የማመንጨት እና ራሳቸውን ችለው የመንቀሳቀስ ሞራላቸው ተሰልቧል። በዚህም ምክንያት ከዓመት ዓመት በራቸውን ዘግተው የሚከርሙ ሆነዋል።

ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ "ነፃ ነን" የሚለውን መፈክር ከፍ አድርገው ሲያዜሙት ይደመጣሉ። ብናጠፋ እንኳን መንግሥት ሊጠይቀን አይቻለውም የሚል አቋም እንዳላቸው በአደባባይ የመናገር ድፍረት ላይም ደርሰዋል። ከዚህም ባስ ባለ መንገድ እነሱ የሚሰፍሩለትና በቁጥጥራቸው ስር ያደረጉት አካል ካልሆነ በስተቀር ሕዝብም ቢሆን ሊጠይቀኝ አይቻለውም የሚል አመራርም እንደተፈጠረ የፓሪስ ኦሊምፒክ አሳይቶናል።

ጠቅለል አድርገን ስንመለከት በእነዚህ የስፖርት ድርጅቶች ውስጥ ተቋም የሚያስመስልና ሥራ መሥራት የሚያስችል ውስጣዊ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስም ይሁን ቁሳዊ ሀብት የለም። አንዳንዶቹ የነበረውንም አፍርሰው ያለ ሙያተኛ ስሙን ብቻ ይዘው ባዶ ቀርተዋል። ስለሆነም በዚህ ቁመናቸው ሕዝቡ የሚፈልገውን የስፖርት ልማትም ይሁን ሀገራዊ ውጤት ማረጋገጥ አይቻላቸውም። ለዚህም ነው መፍትሔው ስርነቀል ለውጥ የሚሆነው።

በድምሩ ስንመለከተው ኢትዮጵያ በፓሪስ ኦሊምፒክ ከወርቅ የራቀችው የስፖርት ተቋማት ብቃት የሌላቸው (Inefficient) እየሆኑ በመምጣታቸው፣ የስፖርቱ የአሠራር ሥርዓት (System) በየደረጃው በብልሹ አሠራር በመዋጡና Corrupted በመሆኑ፣ የስፖርተኛው ምልመላና ሥልጠና እጅግ በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ፣ ስፖርቱ የእርስ በእርስ መበቃቀያና የብሽሽቅ ሜዳ እየሆነ በመምጣቱ፣ ስፖርቱ የተወሰኑ ግለሰቦች በማን አለብኝነት ብቻ የሚዘውሩት የግል ሀብት (Individual Property) ወደ መሆን በመሸጋገሩ፣ በአመራር (Leadership) ችግር....ወዘተ ነው።

ማህፀነ ለምለም የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ከጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ጀምሮ በታምራት ቶላ በፓሪስ ኦሊምፒክ እስከተገኘው የወርቅ ሜዳሊያ ድረስ በርከት ያሉ ጀግኖችን በሩጫው መስክ ለዓለም አስተዋውቃለች። ዓለም ኢትዮጵያውያን በሚሳተፉባቸው የረጅም ርቀት ውድድሮች መወዳደር እስከሚፈራ ድረስ የራሷን አረንጓዴ ጎርፍ ፈጥራ የውድድር መድረኩን በድል አጥለቅልቃው ኖራለች። ያ የአሸናፊነት ስሜትና ድል ለኢትዮጵያውያን ዋጋው እጅግ ብዙ ነው።

ነገር ግን ይህ የሀገር ፍቅርና አንድነት የሚታይበት አትሌቲክሳችን እ.ኤ.አ በ2016 በተካሄደው የሪዮ ኦሊምፒክ ተጎድቶ፤ በ2020 የቶኪዮ ኦሊምፒክ ታሞ በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ የሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ታይቷል።

ከጅምሩ ብዙ እሰጣ ገባዎች በተከሰቱበት የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ በ1 ወርቅና በ3 የብር ሜዳሊያዎች ከዓለም 47ኛ ደረጃን ይዛ ጨርሳለች። ይህን ተከትሎ በኢትዮጵያውያን ዘንድ መከፋት ሆኗል።

ከላይ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥልጠና ሂደታችን ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ ባለመሆኑ፣ በአንድ ፊልድ የሚሮጡ አትሌቶች በተለያዩ አሠልጣኞች ስር መሠልጠናቸውና መገፋፋት በመኖሩ፣ ውድድሮች ከመካሄዳቸው በፊት ስለውድድሩ ቦታ ጥናት ተደርጎ ቦታውን በሚመስል ቦታ ሥልጠና መስጠት ባለመቻሉና የጋራ ሥራ የመሥራት እንዲሁም የጋራ ውጤት የማምጣት ተነሳሽነት በዘርፉ በመጥፋቱ ለውጤቱ መዳከም እንደተጨማሪ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

አሠልጣኞችና የፌዴሬሽን አመራሮች እንዲሁም የኦሊምፒክ ኮሚቴው ቀድመው ውድድሩን ላናሸንፍ እንችላለን እና ተሳትፎ በቂ ነው እያሉ በሚናገሩበት ሂደት አልፎ ውጤት መጠበቅ ከባድ ነው።

በስፖርቱ ውስጥ በዘርፉ እውቀት ያላቸው ሰዎች ገብተው እንዲሠሩ መንግሥትም ቢሆን ጫናዎችን ማሳደር አለበት። ዕውቀትና ልምድ አንድ ላይ ካልተጣመሩ ውጤት እንደማይገኝ የዘንድሮ የፓሪሱ ኦሊምፒክ ጥሩ ማሳያ ነው።

በተለይ የቡድን መንፈስን የሚረብሹ ሂደቶችን በማስወገድ ግልፀኝነት የተሞላበት የስፖርት ተቋምና አሠራር ሊፈጠር ይገባል። አትሌቶች ወደ ውድድር ሲገቡ ሥነ-ልቦናቸው ሊጠበቅ ግድ ይለዋል። የርስ በርስ ፀብና መገፋፋት ባለበት ሁኔታ ከአትሌቶቹ ውጤትን መጠበቅ አይቻልምና ነው።

ኢትዮጵያ በተከታታይ ሦስት ኦሊምፒኮች በሪዮ፣ ቶኪዮ እና ፓሪስ በየእያንዳንዳቸው ከአንድ ወርቅ በላይ ማሳካት አልቻለችም። በዘንድሮው የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ በሁለት ርቀቶች በቀነኒሳ በቀለና በቲኪ ገላና ተይዘው የነበሩ ሪከርዶችን ለዩጋንዳና ለኔዘርላንድ አሳልፋም ሰጥታለች።

የዘንድሮ የኦሊምፒክ ውጤት የተቋምም፣ የአሠራርም ውድቀትን ያሳያል። ኦሊምፒክ ለኢትዮጵያውያን ከሜዳሊያ ባለፈ የጽናት እና የአይበገሬነት ምልክት ነው። የኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ታሪክ ለአፍሪካውያን የአሸናፊነት ሥነ-ልቦናን የከፈተ ነው። መድረኩ ሀገርን በማስተዋወቅ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። አትሌቲክስን ከውጤት ባለፈ ከማንነታችን እና ከታሪካችን ጋር በአግባቡ አቆራኝቶ ማየት ተገቢ ነው።

የአሸናፊነትን መንፈስን በትውልዱ ለማስረጽ የውጤታማ አትሌቶቻችንን አብነት ማሳወቅ በእጅጉ ጠቃሚ ይሆናል። የሙያ ሥነ-ምግባር፣ ትጋት እና ሀገርን ማስቀደምን ከኢትዮጵያ ድንቅ አትሌቶች ሕይወት መማር ይቻላል። በፓሪስ ኦሊምፒክ ኅብረተሰቡ ቅሬታ የገባው ሕዝቡ የለመደውን ወርቅ ባለማግኘቱ ብቻ ሳይሆን በልዑኩ ውስጥ ያለው ልዩነት እና ያልተገባ አሠራር አደባባይ በመውጣቱ ጭምር ነው።

ምንም እንኳን በስፖርት ውስጥ ማሸነፍና መሸነፍ ያለ ቢሆንም አንበገርም፣ በቅኝ አልተገዛንም እያልን፤ በውድድሮቹ ለነጮች እጅ ስንሰጥ ሕዝቡን በተሸናፊነት ስሜት ቁጭት ውስጥ አስገብቶታል። የዘንድሮ ውጤት ስፖርቱ በተቋም እና በሥርዓት (ሲስተም) ደረጃ ያለበትን ውድቀት በግልፅ አሳይቷል። በስፖርት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ብልሹ አሠራሮች ለሀገር ውጤት ሲባል ሊስተካከሉ ይገባል።

ስፖርት በአግባቡ ከተያዘ ለማኅበረሰባዊ አንድነት የማይተካ ሚና ሲኖረው፤ በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ የልዩነት ምንጭ እና ማስፊያ በመሆን ማኅበረሰቡ ላይ ተጨማሪ ችግር እንደሚጋርጥ ግልፅ ነው።

አትሌቲክሱ ላይ ያሉ ሁለንተናዊ ጉዳት የሚያመጡ ችግሮችን መናገርም የዜግነት ግዴታ መሆን አለበት። መንግሥትም በስፖርት ዘርፉ ላይ ያሉ የዕድገት ማነቆዎች ሊታረሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለበት ሁሉ።

# ስፖርት

## የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ዋና ጽሕፈት ቤቱን በኢትዮጵያ ከፈተ

ዓለማየሁ ግዛው

የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ዋና ጽሕፈት ቤቱን በአዲስ አበባ አንድነት ፓርክ ከትናንት በስቲያ በይፋ አስመርቆ ከፍቷል። በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይም የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ፣ የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ዋና ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ መከፈቱ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ መከፈቱ የቦክስ ስፖርት እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ከማስቻሉም ባሻገር በሥራ እድል ፈጠራም ሚናው የጎላ መሆኑን ሚኒስትሯ ተናግረዋል። በሁሉም ስፖርቶች ተወዳዳሪዎችን ለማፍራት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ መከፈቱ የቦክስ ስፖርትን እንደሚያነቃቃ ገልጸዋል፡፡ በስፖርት ዲፕሎማሲ ከተለያዩ የአህጉሪቱ ክፍሎች ለመጡ ሀገራት ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል፡፡ መንግሥት ለስፖርቱ ከመሠረተ ልማት ግንባታ ጀምሮ ቁርጠኛ በመሆኑ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ቀጣይ ሥራዎችን አቅዶ ለመሥራት ጥረት እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እና የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እያሱ ወሰን በበኩላቸው፤ ጽሕፈት ቤቱ አዲስ አበባ ላይ እንዲከፈት መንግሥትን ጨምሮ እገዛ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡ በእለቱ ምሽት ላይ በዓድዋ ሙዚየም የተካሄደውን የአፍሪካ ኢንተርናሽናል ቦክሲንግ አሶሲየሽን (IBA) ውድድርን ጨምሮ ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በማዘጋጀት ለስፖርቱ እድገትና ተወዳጅነት እንደሚሠሩም ገልጸዋል።



በአዲስ አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የቡጢ ፍልሚያ ሁለት ኢትዮጵያውያን ቦክሰኞች ጥሩ ተፎካካሪ ነበሩ፤

የስፖርት ቱሪዝምን ከማስፋት ከሀገር ገጽታ ግንባታ እና የውጪ ባለሀብቶችን ለመሳብ እንደሚያስችልም ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም ስፖርተኞችን ተጠቃሚ ከማድረግና የውጪ ምንዛሬ ወደ ሀገር በማምጣት ትልቅ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል። በአፍሪካ ስም ደላሎችና ሌሎች አካላት እስከ አሁን እየተጠቀሙ እንደነበረና ያንን በማሸነፍ ውድድሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ እንዲካሄድ መደረጉንም አስረድተዋል፡፡ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም መሰል ትላልቅ ውድድሮችን ለማድረግ እንደታቀደ ገልጸዋል፡፡

በምረቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፤ የኪነ-ጥበብ ሥነ-ጥበብ ፈጠራ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ነፊሳ አልማህዲ፣ እንዲሁም የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እና የቦርድ አባላት እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በዓድዋ ሙዚየም ከ51 እስከ 96 ኪ.ግ ክብደት ባሉ የውድድር ዘርፎች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የቦክስ ፍልሚያ አድርገዋል፡፡ በውድድሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ7 ሀገራት የተወጣጡ ቦክሰኞች ተሳትፈዋል። አንድ የሴቶችና ስድስት የወንዶች ፍልሚያ ፕሮፌሽናልና ሁለት ሴሚ ፕሮፌሽናል ግጥሚያዎችም ተከናውነዋል።

ኢትዮጵያን በ60 ኪሎ ግራም የወንዶች ፍልሚያ የወከለው አቡበከር ሰፋን ከ ጋናው ጆሴፍ ኮሜይ ጋር በ 6 ዙሮች ፍልሚያ ጥሩ ፍክክር አድርጎ ተሸንፏል፡፡ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ ተመስገን ምትኩ በ75 ኪሎ ግራም ከሞሮኮው ቦክሰኛ ያሲን ኢሎራዝ ጋር የ3 ዙር ፍልሚያ አድርጎ ድል አልቀናውም።

በወንዶች 80 ኪሎ ግራም ከባድ ሚዛን ፍልሚያ ታንዛኒያዊው ዩሱፍ ቻንጋላዌ ከዲሞክራቲክ ኮንጎው ፒታ ካቤጂ በ8 ዙር ተፋልሞ አሸናፊ ሆኗል፡፡ 8 ዙሮችን በፈጀው የወንዶች 48 ኪሎ ግራም ቀላል ሚዛን ፍልሚያ ሩሲያዊው ኢድመንድ ኩሁዶዮን ሜክሲካዊውን ዳንኤል ቫላዴራዝ ገጥሞ አሸናፊ መሆን ችሏል፡፡ በወንዶች ተመሳሳይ 48 ኪሎ ግራም ቀላል ሚዛን ኡዝቤኪስታናዊው ኖዲርጆን ሚዝራክሜዶቭ ከካዛኪስታኑን ቴምራትስ ዝሁስፖቭ በ8 ዙር ያደረጉት ፍልሚያ በካዛኪስታናዊው ቡጢኛ አሸናፊነት ተጠናቋል።

በወንዶች 80 ኪሎ ግራም ከባድ ሚዛን ፍልሚያ ታንዛኒያዊው ዩሱፍ ቻንጋላዌ የዲሞክራቲክ ኮንጎውን ፒታ ካቤጂ በ8 ዙር ተፋልሞ አሸንፎታል፡፡

በወንዶች 51 ኪሎ ግራም ቀላል የቀበቶ ፍልሚያ ዛምቢያዊው ፓትሪክ ችንዬምባ ጋናዊው አሎቲ ቲዮፊለስ በ4 ዙሮች ተፋልሞ የቀበቶ አሸናፊ መሆን ችሏል። በሴቶች መካከል በተካሄደው የ75 ኪሎ ግራም መካከለኛ ሚዛን ፍልሚያ ሞዛምቢካዊቷ ክራዲይ አዶሲንዳ ግራማኔ በናይጀሪያዊቷ ፓትሪሺያ ምፓታ በ 6 ዙር ፍልሚያ ተረትታለች።